ነበር:: ስለዚህ ልብስ ከፈጣሪ አይበልጥምና አለባበስን በተመለከተ «ፈጣሪዬ ከኔ የሚሻው ነገር ምንድር ነው?» እያሉ በአግባቡ መመላለስ ይገባል::

ሰ. ሕይወት በእንቅስቃሴ የተሞላች ናት:: ከቤት ለአንድ ዓላማ ብለሽ ከወጣሽ በኋላ እግረ መንገድሽን ቤተ ክርስቲያንም ሆነ ሌላ ቦታ መድረስ ያስፈልግሽ ይሆናል:: ታዲያ አለባበስሽ ማንኛውንም ነገር ከማድረግ የማያግድሽ ሁለገብ እንዲሆን ለምን አትጥሪም? ለአንቺም ቢሆን እኮ የምታከብሪያቸውን ሰዎች ስታዪና በእግዚአብሔር ፊት ለመቆም ወደ ቤተ ክርስቲያን ስትሄጂ በመሳቀቅ ከምታልቂ አንድ ፊቱን በእግዚአብሔርና በመልካም ሰዎች ዘንድ የተወደደ አንድ ወጥ የአለባበስ መንገድ ብትከተዪ መልካም ነው::

ሸ. ልብስ ስትለብሺ በእንቅስቃሴ ወቅት እንዴት እንደምትሆኚ አስቢ እንጂ እንደ ልብስ ማሳያ አሻንጉሊት ይመስል የሰቀሉብሽን ወይም ያምርብሻል ያሉሽን ሁሉ አትልበሺ:: አንቺ እኮ! በመኪና ቁጭ ብለሽ የምትጓዢ፣ በቢሮ ቁጭ ብለሽ የምትጽፊ፣ አጎንብሰሽ የወደቀ የምታቀኚና ልብስ የምታጥቢ በአጠቃላይ በእንቅስቃሴ የተሞላ ሕይወት ያለሽ ፍጡር ነሽ:: ታዲያ በነዚህ እንቅስቃሴዎችሽ ውስጥ አጭርና ጠባቃ ልብስ ብትለብሽ ለሌሎች እይታ የምታጋልጫቸውን ሕዋሳቶችሽንና ሊፈጠርብሽ የሚችለውን አንዳንድ መጥፎ ገጠመኝ ለምን አታስተውዪም:: እኔ በግሌ አጭር ልብስ ለብሶ ማርዘም ላይቻል ሲጎትቱ ከመዋል ረጅሙን መርጦ መልበስ ይሻላል እላለሁ::

ቀ. አንዳንድ ወጣቶች ኋላ ቀር መስለው እንዳይታዩ በጣም አዲስ ከሆነው ፋሽን ጋር መራመድ እንደሚገባቸው አድርገው





ያስባሉ:: ምን ጊዜም ከመጠን ያለፈ «ወግ አጥባቂ» በመሆንና በጣም «ዘመናዊ» በመሆን መካከል አንድ አማካይ ቦታ ይኖራል:: ይህን መሀከለኛነት ከያዝሽ ሁል ጊዜ ጥሩ አለባበስ ይኖርሻል:: በየጊዜው ለሚመጣው የፋሽን ለውጥ ተገዥ ከመሆንም ትድኛለሽ::

በተጨማሪም ስለ ፋሽን በጣም በመጨነቅሽ የምትጠቅሚው ማንን ነው? መልሱ ራስሽን ሳይሆን ፋሽኖችን የሚያቀርበውንና የሚያበረታታውን የንግዱን ዓለም ነው:: እነርሱ አንድ ዋነኛ ዓላማ አላቸው፤ እርሱም ገንዘብ ማግኘት ነው:: በእነርሱ ሥራ ውስጥ የሰይጣንን ሚና ከተመለከትሽ ደግሞ ዓላማው በብልሹ አለባበስ ምክንያት በዓለም ላይ የሥነ ምግባር ጉድለት እንዲንሰራፋ፣ ስለ እግዚአብሔር ማሰብ በቁሳዊ ነገር እንዲተካ ማድረግ ሆኖ ታገኝዋለሽ:: ስለዚህ ሁልጊዜ ፋሽን ተከታይ ከሆንሽ አንቺ ምንም ሳትጠቀሚ ገንዘብሽን ጨምሮ የምታጫቸው ነገሮች በርካታ ናቸው::

በ. ስለራሳቸው በጣም የሚኩሩ ሰዎች ኩራታቸውን የሚያሳዩት ብዙ ጊዜ ስለ አለባበሳቸው ከመጠን በላይ በመጨነቅ ነው:: በልብሳቸው ወይም ገመልካቸው ሁል ጊዜ «ሌሎችን አስንቀው» ለመታየት ይፈልጋሉ:: ይህንንም ቅዱስ ዮሐንስ አፈ ወርቅ እንዲህ ሲል ገልጾታል:- «ከመ ትዘነሪ መትትመክሒ በላዕለ ብዙኃት አንስት ነዳያት ወትትዐበዪ በቅድመ አዕይንቲሆን ወትምስዊ አልባቢሆን ወታድውዪ ነፍሳቲሆን ወትወስኪዮን ንዴተ በዲበ ንዴቶን» ይህም አንቺ ሴት አጊጠሽ መውጣት የምትፈልጊው «ልብስ በሌላቸው በድሆች ላይ ልትመኪ፣ በፊታቸው ልትታበዪ፣ ልቡናቸውን በቅንአት እንደ ሰም ልታቀልጪ፣ ሰውነታቸውን

በቅንአት ልታሳምሚና በኃዘናቸው ላይ ኃዘን ልታመጪባቸው ወደሽ ነው እንጂ በሌላ ምክንያት አይደለም።» ማለት ነው። አንቺ ራስሽ «ዝንጥ» ያልሽ ጊዜ እንዲህ ዓይነት ስሜት ተሰምቶሽ አያውቅም? ተግ.ዮሐ28

ውድና ጌጠኛ ልብስ መልበስ ያኮራሻል? ይህ የሚያኮራሽና ከሌላው ሰው የበለጥሽ መስሎ የሚሰማሽ ከሆነ ሰነፍ ሴት ነሽ። አላዋቂ በመሆንሽም ታሳዝኚኛለሽ እንጂ አታስጎመጂም። ምክንያቱም እንኳን ዐዋቂው የሰው ልጅ ይቅርና ፈረስና በቅሎ እንኳን የሰው ያህል ዕውቀት ሳይኖራቸው በጣም የሚደሰቱት ጌጣጌጥ አድርገውላቸው ከሚነዷቸው ይልቅ አራግፈው ሲያቀሉላቸው ነው። ስለዚህ ዐዋቂ የሚባል የሰው ልጅ ወርቁን ሐሩን በራሱ ቢሸከመው በወገቡ፣ በደረቱ፣ በእጁና በጣቱ ቢያጠልቀው በአንገቱም ቢያንጠለጥለው ሊያፍር እንጂ ሊኮራ አይገባውም ነበር።

ያደረገው የወርቅና የሐር ጌጥ ዕወቀትና ሕይወት የሌለው ፍጡር በመሆኑ ነው እንጂ ኩራት የሚገባው ለእርሱ ነበር። ለባሕርይው የማያሻው ነገር ከተጫነበት ሰው ይልቅ ጌጡ ቢኩበር ምን ይደንቃል? በላዩ የተቀመጠበት ሳይኮራ ተሸካሚው የሰው ልጅ መኩራቱና መደሰቱ እጅግ የሚያሳዝንና ዐላዋቂነት ነው። ተመልካቾችም ስለዚህ ሽክም ምክንያት ሊያዝኑለት ሲገባቸው ቢቀኑበት ወይም ቢያከብሩት ቅዱስ ያዕቆብ ለወርቅና ለብር በመሳሳታቸው የነቀፋቸው ከንቱዎች ናቸውና አይመስገኑም። ዐዋቂ ግን ሌላውን ባለው ወርቅና ብር ብዛት አያከብርም። ለራሱም ቢሆን በሀብቱ ብዛት እናደሚከበር አያስብም አይቀበለውምም።





በሌላ አቅጣጫ ስንመለከተው ደግሞ አንዳንድ ጊዜ ስለ ልብስ «ግድ የለሽ» መሆንም ኩራትን ወይም ራስ ወዳድነትን ሊያሳይ ይችላል። በአለባበሱ የተዝረከረከው ግለሰብ ስለ አለባበሱ ግድ የለሽ የሆነው በስንፍና ምክንያት ሊሆን ቢችልም አለባበሱ በሌሎች ላይ ለሚያሳድረው ተጽዕኖ «ምን ቸገረኝ!» የሚል ዓይነት ዝንባሌ ያለው ሰው መሆኑን ሊጠቁም ይችላል።

ተ. እኛ ራሳችንን ከምንመለከተው በላይ ሌሎች ሰዎች ይመለከቱናል። ታዲያ ሌሎች ሲመለከቱን መልካም ነገር ከእኛ እንዲያገኙ መጣር የለብንምን? ይህም ስለ ስሜታቸው እንደምንጠነቀቅላቸው የሚያሳይ መሆን አለበት። ብዙ ክርስቲያኖች ግን ነገረ ሥራቸው በሙሉ ወዳጆቻቸው ስለራሳቸው በሚያስቡበት ጊዜ እንዲሸማቀቁ የሚያደርግ ነው። በዚህም ተግባራቸው «እያንዳንዳችን እንድናንጸው እርሱን ለመጥቀም ባልጀራችንን ደስ እናሰኝ» በማለት ሐዋርያው የተናገረውን ምክር ቀኑን ሙሉ ሲሽሩት ይውላሉ። ሮሜ 12፥2

ቸ. አንቺ ሴት እስኪ ነፍስሽን ትሕትና አስተምሪያት። ሁልጊዜ ደምቆና አሽብርቆ መታየት ብቻ ሳይሆን ተራና መናኛ ልብስን መልበስንም ተ ማመጂ። «ሞትን የምታለብስና ወደ ሲኦል የምታወርድ አፍአዊ ጌጥን» ከልክ በላይ አትውደጂ። ይህ በነፍስ እንደ ማጌጥ በእግዚአብሔር ፊት አያኮራሽምና። ለአፍአዊ ጌጥ የማትጓጓ ሴት ዘውድ ከደፋ ንጉሥ ትበልጣለች። እንዴት? ቢባል ሰው ሁሉ ለቁሳቁስ ሲገዛ እሷ አትገዛምና።

ነ. አንዳንድ ሰዎች ስለ አለባበስ ባይሰበክ ይመርጣሉ። ብዙዎች ደግሞ «ለምን ስለ ሌላ ነገር አታስተምሩም?» ከዚህ ይልቅ ብዙ

እንገብጋቢ ርእስ ጉዳይ የለምን?» ይላሉ:: እርግጥ ቅድሚያ የሚሰጠው ነገር ይኖር ይሆናል፣ ሆኖም የአለባበስ ጉዳይም በክርስትና ዐቢይ ነገር ነው:: ያ ባይሆን ኖሮ ሐዋርያትም ሆኑ ሊቃውንት ስለ አለባበስ ብዙ ባልጻፉ ነበር:: ይህ ጉዳይ ተራ ነው የምትዪ ከሆነ አለባበስሽን በማስተካከል ተራነቱን አንቺ ራስሽ አስቀድመሽ ማሳየት ይገባሻል:: ካልሆነ በጉዳዩ በየጊዜው ላለመገሠጽ ብለሽ ትምህርቱን ማናናቅሽ አስተዋይ አያደርግሽም::

## አለባበስሽ ስለ አንቺ በደንብ ይናገራል!

አለባበስሽና ውጫዊ ቁመናሽ ከውስጥሽ ምን ዓይነት ሰው እንደ ሆንሽ መቶ በመቶ ባያስረዳም የቀረበ ግምት ለመስጠት ይረዳል:: ሕፃን ሳለሽ አለባበስሽ ምን ዓይነት ሰው እንደሆንሽ ብዙም አይናገር ኖሮ ይሆናል:: ልብሶችሽን የሚመርጡልሽና ፀጉርሽንም የሚያበጥሩልሽ አሳዳጊዎችሽ ናቸውና:: እያደግሽ ስትሄጂ ግን ልብስ ስለ መምረጥ፣ ስለ ፀጉር አያያዝና ስለመሳሰሉት የራስሽን ምርጫ እንድትከተዪ ይተውሻል:: ከዚያ ወዲያ የራስሽ ምርጫ መታየት ጀመረ ማለት ነው:: ስለዚህ ቁመናሽና አለባበስሽ በውስጥሽ ምን ዓይነት ሰው እንደሆንሽ ማንጸባረቅ ጀምሯል:: እስኪ ይህን ንባብ ገታ በማድረግ የሰውነትሽ አቋምና አለባበስሽ ስለ አንቺ ምን እንደሚናገር ለአፍታ ቆም ብለሽ አስቢው::

አለባበስሽ በእርግጥ ስለ አንቺ ስለሚናገር ከአንድ ዓይነት ቡድን ወይም ክፍል ጋር ያስመድብሻል:: ብዙ ሺህ ዓመታት ወደኋላ መለስ ብለን ብንመለከት ይህንን እውነታ ከመጽሐፍ ቅዱስ እንረዳለን:: ለምሳሌ በነገሥት መጽሐፍ ውስጥ የንጉሥ አካዝያስ መልእክተኞች እርሱ ከላካቸው በኋላ አንድ ዓይነት ሰው





ማግኘታቸውንና እርሱም በበኩሉ መልሶ መልእክት እንደላካቸው ተመልሰውም ለንጉሡ እንደተናገሩ ተጽፏል:: ንጉሡም «የሰውየው መልክ ምን ይመስላል» ብሎ ጠየቃቸው አለባበሱን በገለጹለት ጊዜ ወዲያውኑ «ኤልያስ ነው» አለ:: እንዴት ዐወቀው ቢሉ ኤልያስ ነቢያት የሚለብሱትን ዓይነት ልብስ ይለብስ ስለነበረ ነው:: 2ነገ1÷2-6

በእርግጥ በነቢይነት መታወቅ ክብር ያለው ነገር ነው:: ይሁን እንጂ ቀጥሎ የሚጠቀሰው የመጽሐፍ ቅዱስ ቃል ምሳሌ አለባበስ አንድን ሰው በወራዳና በተነወረ ተግባርም ሊያሳውቀው እንደሚችል ያሳያል:: የይሁዳ ምራት ትዕማር የፈለገችውን ለማግኘት ዓላማ አድርጋ የመበለትነት ልብሷን አወለቀችና መጎናጸፊያና መሸፈኛ ለብሳ ከመንገድ ዳር ተቀመጠች:: አማቷ ይሁዳ በዚያ መንገድ ሲያልፍ «ጋለሞታ መሰለችው ፊትዋን ሸፍና ነበርና» በማለት መጽሐፍ ቅዱስ ይተርካል:: ትዕማርን አለባበሷ በጊዜው የነበሩትን ጋለሞታዎች አስመስሏት ነበር:: ዘፍ38÷13-15

እንደ ቀድሞ ጊዜ ሁሉ ዛሬም ምንም እንኳን ያን ልብስ የሚለብሱ ሰዎች የሚያደርጉትን ባናደርግና የሚያምኑትንም ባናምን አለባበሳችን ግን እንደ እነርሱ ከሆነ ከእነርሱ ጋር በአንድ ሊያስመድበን ይችላል:: ሌሎች ከአለባበሳችን ተነሥተው ስለ እኛ እንዲህ በማሰባቸውና በመገመታቸው ልንፈርድባቸው እንችላለንን? ሌሎች አሳባቸውን እንዲለውጡ ከማድረግና እኛ አለባበሳችንን ከማስተካከል የቱ ይቀላል? በቀላሉ ሲገለጽ አሳብን ከመቀየር ልብስን መቀየር አይቀልምን?

በተገቢው መንገድ የሚሹትን አፋአዊ ጌጽ ካላገኙ በመስረቅ፣ በመዋሸትና ፍላጎታቸውን ሊያሟሉ ለሚችሉ ሀብታም ሰዎች በመገዛት ያሟሉታል። ይህ መገዛታቸው ልክ በማጣቱ ሐሳባቸው ይሟላላቸው ዘንድ ለዝሙት ከመንበርከክና ከመግደል አንሥቶ ለማንኛውም የኃጢአት ተግባር ወደ ኋላ አይመለሱም። ሊያገቡት የመረጡትንና ያጩትንም ሰው የጌጥ አምሮታቸውን ባለሟሟላቱ ብቻ እስከ መካድ የሚደርሱበት አጋጣሚ እጅግ ብዙ ነው። በዚህ ምክንያት አፍአዊ ጌጽ መውደድን እንደ ጨካኝ ጌታ ስንቆጥረው ጌጽ ወዳጅዋን ሴት ደግሞ የሥጋና የዓለም ታማኝ ሎሌ እንላታለን። ለምን ቢባል ጌጥ በመውደዷ ብቻ የማትፈልገውን ኃጢአት ሁሉ ትሠራለችና።

አንቺ ሴት እንደ ሌሎች ሴቶች ለማጌጥ አቅም በማጣትሽ ለምን ታዝኛለሽ? ፈጣሪሽ ለጌጣጌጥ በባርነት ከመገዛት ነጻ ስላወጣሽ ታዝኛለሽን? አንድ ሰው መዝገቡን ተግተሽ አንድትጠብቂ ቢያዝሽ እጅግ ታዝኚ ነበር። ከዚህ ይልቅ ግን የጌጣጌጥሽን ጉዳይ ለመሟላት የምታደርጊው ጥንቃቄና ዝግጅት ይከብዳል። ታዲያ ለጌጣጌጥ በመገዛት ራስሽን በጽኑ ማሠሪያ ለምን ታሥሪዋለሽ? ጠፍቶብሽ ከመደንገጥ፣ እዘረፋለሁ ከማለት፣ ግድ ለማያስፈልግ ነገር ከፍተኛ ባጀት ከመመደብ፣ ጊዜ ከማባከን፣ በጌጥ ምክንያት የሰው እጅ ከማየት፣ ወዘተ ነጻ እንደ መሆን ምንም አይገኝም። ማጌጫ አጣሽ ማለት ከእነዚህ ሁሉ ክፉ ነገሮች ነጻ ወጣሽ ማለት ነውና።

ጌጽ መውደድ ባርነት ብቻ ሳይሆን «ጣዖት አምልኮ»ም ነው። ነፍስ በጽኑ ፍቅር የታሠረችበት ከሆነ ሁሉም ነገር ወደ አምልኮት ይሄዳልና። ታዲያ አንቺ ያለ ጌጽ ምንም ነገር የማይሆንልሽ፣





ጌጥሽን ልጆችሽና አገልጋዮችሽ እንኳን ሊነኩት ሊያዩት የማታደርጊቸው ከሆነ፣ ለራስሽ እንኳን ልታጌጪበት የምትሳሽለት፣ ለሌላ ማዋስማ ፈጽሞ የማይታሰብ ነገር ከሆነብሽ ከዚህ የበለጠ «ጣዖት አምልኮ» ከወዴት ይመጣል? በቀን ዐሥር ጊዜ ማጥን ከፍተሽ የምትመለከቺው፣ ዕጣን የምታጥኚው፣ ሽቶ የምትቀቢው፣ አጥፈሽ የምትዘረጊው፣ የምታናፍሽው፣ ብታውሺው እንኳን ጠ ባይሽን ዐውቀው «ያጅሪት ገንዘብ» እያሉ ያዋስሻቸው ሰዎች እንዳንቺ የሚጠነቀቁ ከሆነ ትንሽ ቢበላሽባቸው ደግሞ ጥፋታቸውን የማትታገሻቸው ከሆነ ያ ነገር ላንቺ «ጣዖት» ነው ቢባል ይበዛበታልን? በፍጹም አይበዛበትም። ምክንያቱም መምለኪያነ ጣዖታት (ጣዖታትን የሚያመልኩ ሰዎች) ጣዖትን እንደሚንከባከቡት አንቺም ጌጣጌጥሽን የምትንከባከቢው እንደነርሱ ነውና።

በተመሳሳይ መልኩ ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ ለአፍአዊ ጌጽ የሚሳሱ ሰዎች ከጣዖት አምላኪ ጋር እንደሚቆጠሩ የቅዱስ ጳውሎስን ቃል ጠቅሶ ተናግሯል። «እስኩ ንግረኒ ኢኮነሁ ርቱዐ ቃለ ሐዋሪያ ሶበ ይሰምዮ ለስሱዕ ከመ መምልኬ ጣዖት» ይህም ወደ አማርኛ ሲመለስ «እስኪ ንገረኝ ሐዋሪያው ጣዖት የሚያመልኩትን በነቀፈበት አንቀጽ «አው ዐማፂ (ዐመፀኛም ቢሆን)» ብሎ በምንዝር ጌጥ (በትውዝፍት) እና በፍቅረ ንዋይ የታሠሩትን ሰዎች አየይዞ መንቀፉ የሚገባ አይደለምን? ጣዖት አምላኪዎች ጣዖታትን እንደሚያከብሯቸው «ከማሁ እሉሂ ያከብሩ አልባሰ ወንዋየ፤ እንዲሁ እነዚህም ልብስንና ገንዘብን ያከብራሉና» ማለት ነው። ተግሣጽ ዘዮሐ አፈ.20

እስራኤላዊያን ጭቃ በመርገጥ ኖራ በመውቀጥ ለግብፅ ንጉሥ ይገዙ ነበር:: እኅቶቻችንም ርጉም ሰይጣንን ለማስደሰት ለአፋዊ ጌጣጌጥ ብዙ ይጨነቃሉ:: ከፈርዖን አገዛዝ ለአፋአዊ ጌጣጌጥ መገዛት ይከፋል:: ያ ሥጋዊ ነውና፤ ለጌጣጌጥ መገዛት ግን በቀጥታ ለዲያብሎስ መገዛት ነው:: ሆኖም እግዚአብሔር የራሔልን ዕንባ ተመልክቶ እስራኤላዊያንን እንደታደጋቸው እኛም ንስሐ ብንገባና ስለ ኃጢአታችንም መሪር ዕንባን ብናነባ የነፍሳችንን ኀዘን ተመልክቶ ለቁሳቁስ ከመገዛት ፈጣሪያችን ነጻ ያወጣናል:: ዕንባችንን አይቶ የሚልክልን ጸጋም ሊቁ «ይፌኑ ለነ ቃሎ ወረድኤቶ ወፈሪሆተ ዚአሁ» እንዳለ «ቃሉን ትእዛዙን ፣ ረድኤቱን እርሱን መፍራትንና ሰውን ማፈርን ያሳድርብናል እንጂ ፤ ሙሴና አሮንን አይደለም::» በዚህ ጊዜ በግብፅ ከተመሰለች ኃጢአት ሙሉ በሙሉ ነጻ እንወጣለን ፤ መልካምና ክፉንም ለይተን እናውቃለን::

## «ሴት የወንድ ልብስ አትልበስ» ሲል ምን ማለቱ ነው?

መጽሐፍ ቅዱስ «ሴት የወንድ ልብስ አትልበስ ወንድም የሴትን ልብስ አይልበስ ይላል::» ዘዳ22፥5 ይህን የእግዚአብሔር ቃል «ሴት ሱሪ አትልበስ ማለቱ ነው» በማለት የሚፈቱት አንዳንዶች አሉ:: ነገር ግን ይህ ቃል ምሥጢሩ ከዚህም በላይ ከፍ የሚልና «ሴት ወንድነትን አትላበስ ወንድ ደግሞ ሴትነትን አይላበስ ሁለቱም በተፈጠሩበት ጾታ ጸንተው ይገኙ» ማለትም ይሆናል:: ምክንያቱም ሴትነታቸውን የሚያማርሩ «ዘር ላቀብል» እስከ ማለት የሚደርሱ እጅግ ብዙ «ወንዳ ገረድ» ሴቶች መኖራቸው ይታወቃል::





ከወንዶችም ደግሞ «ዘር ልቀበል፣ ላምጥ፣ ልውለድ» የሚሉ ወንዶች በርካታ ናቸው:: ይህ ጎዳና «በአምላካችን በእግዚአብሔር ዘንድ የተጠላ ነውና» መጽሐፍ ቅዱስ ሴት የወንድን ወንድ ደግሞ የሴትን ልብስ አይልበስ ማለቱ እውነት ነው:: ዘዳ 22፥5

«ሴት የወንድ ልብስ አትልበስ» ሲል ሱሪ አትልበስ ማለቱ ብቻ ከሆነ «ከሁለት ዓይነት ነገር (ቀለም) የተሠራ ልብስ አትልበስ» ሲልስ ምን ማለቱ ነው? የሚል ጥያቄ ያስነሣል:: እስኪ ንባቡን ቆም አድርገውና ከላይ እስከ ታች የለበስከው ልብስ ስንት ዓይነት ነገር (ቀለም) እንዳለው ቁጠረው:: ታዲያ ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ያለው ይህን አለባበስህን ለመንቀፍ ነውን? አይደለም:: «ከሁለት ዓይነት ነገር (ቀለም) የተሠራ ልብስ አትልበስ» ማለቱ ሁለት ዓይነት ሰብእና አትላበስ:: በተጨማሪም «በአንድ ራስ ሁለት ምላስ» እንደሚባለው ቃሉና ሐሳቡ ተለዋዋጭ የሆነ ሁለት ዓይነት ሰው አትሁን ማለቱ ነው:: ይህን የመሰለ «ከተልባ እግርና ከበግ ጠጉር በአንድነት የተሠራ ልብስ አትልበስ» የሚል ትእዛዝም አለ:: ስለዚህ መጽሐፍ ቅዱስ አርእስትና ጎዳኙ እየታየ በሚገባ ይተረጎማል እንጂ በዘፈቀደ የሚነገር አይደለምና መጠንቀቅ ያሻል:: ዘዳ22፥11፤ ዘሌ19፥19

ይህ የመጽሐፍ ቅዱስ ቃል በዚህ መልኩ በመተርጎሙ ጠባብ አመለካከት ያላቸው እጅግ በጣም በርካታ ሴቶች ሱሪ ለመልበስ መግቢያ ያገኙ ይመስላቸው ይሆናል:: ምክንያቱም አብዛኞቹ ሴቶች «ሴት የወንድ ልብስ አትልበስ» የሚለውን ቃል የሚረዱት ሴት «ሱሪ መልበስ አይገባትም» እንደሚል ብቻ አድርገው በመሆኑ ነው:: ከዚህ ቀደም «ሱሪ» የማይለብሱ ሆነው ይህን ትርጓሜ በማወቃቸው

ብቻ «ሱሪ» ለመልበስ የሚነሣሡ ሴቶች እውነት አይነገረን ከተነገረን ግን ዋ! የሚል ዓላማ አንግበ ሰልፍ የሚወጣን ሰነፍ ሰው ይመስላሉ::

ከላይ የተጠቀሰው ቃል ትርጓሜውን በዚህ መልኩ በግልጽ ማስቀመጥ ያስፈለገበት ምክንያት የቃሉን ምሥጢራዊ ፍቺ ባለማወቅ ብዙዎች «ሱሪ» በሚለብሱ ሴቶች ላይ ያላቸው አመለካከት የተዛባ በመሆኑ አመለካከታቸውን ለማረም እንዲችሉ ነው:: እንዲህ ዓይነት ሰዎች ፍርድና ትችት ስለሚያበዙ የእነርሱን አስተሳሰብ ለመገሠጽ ትርጓሜው ተጻፈ እንጂ ሴቶች ሱሪ ይልበሱ ለማለት እንዳልሆነ ልብ ማለት ይገባል:: አሁንም ቢሆን ሴቶች ሱሪ አለመልበሳቸው በብዙ መንገድ ጠቃሚ መሆኑንና የመልካም ማንነታቸው መገለጫ መሆኑን መዘንጋት የለባቸውም:: በማኅበረሳባችን ዘንድ ሱሪ የወንዶች ልብስ መሆኑ በአብዛኛው ሰው ዘንድ ታምኖ ሳለ ሴቶች ሱሪ ቢለብሱ አርአያን መለወጥ ስለሆነ ስሕተት ከመሆኑም ባሻገር ተረማማጅ (ተለዋዋጭ) ዐመልንና ባሉበት ነገር ያለመወሰንን ሁኔታ የሚያመለክት ነው::

## ሴቶች «ሱሪ» መልበስ ይችላሉ?

በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ስለ ወንድና ስለ ሴት አለባበስ ብዙ መግለጫዎች አሉ:: ለምሳሌ ከወንዶች አልባሳት ተርታ ከተጠቀሱት ውስጥ መታጠቂያ፣ መደረቢያ፣ መጎናጸፊያ፣ ሰናፊል፣ ቀሚስ፣ እጀ ጠባብ፣ ካባና ድግ ይገኙበታል:: 1ሳሙ18፥4፤2፥19፤ ዳን3፥21፤ ምሳ31፥24፤ ዮሐ19፥23፤ ኢ.ያ7፡21 በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ከተጠቀሱት የሴቶች አልባሳት መካከል ደግሞ የሚከተሉት ይገኙበታል:: እነርሱም፡ ልግም በገላ፣ መታጠቂያ፣ መጎናጸፊያ፣ ራስ ማሠሪያ፣ ቀጸላና ዓይነ ርግብ ናቸው:: ኢሳ3፡20-24





«ሱሪ» ግን በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ለወንዶች ይልቁንም ለካህናት ብቻ ተጠቅሶ እናገኘዋለን:: ዘጸ39፥29 ያም ቢሆን በተለይ በሀገራችን አብዛኛው ማኅበረ ሰብእ «ሱሪ»ን ያለ አንዳች ተደራቢ ነገር መልበስ የወንዶች መደበኛ አለባበስ አድርጎ መቀበሉን ማረጋገጫ አያስፈልገውም:: ስለዚህ ተገቢ ያልሆነን አለባበስ መርምሮ እንኳን «ሱሪ» ይቅርና ቀሚስም ቢሆን አለመልበስ ለሴቶች የተገባ ነው:: ወንዶችም ቢሆኑ ሱሪ ስለ ሆነ ብቻ ሳይሆን በልዩ ልዩ መንገድ መዝኖ ሊያደርጉት የማይገባ ከሆነ መተው ይጠበቅባቸዋል::

በተረፈ ሴቶች «ሱሪ» መልበሱን ካልተውት ሲብስ ነው እንጂ «ሱሪ» በመሆኑ ብቻ ለባሾቹን ከመተቸት መተው ይመረጣል:: እንዲህ የተባለው «ሴቶች ሱሪ መልበስ አይተዉም» በማለት ተስፋ ከመቁረጥ የመነጨ ሳይሆን «ሱሪ» መልበስ እጅግም የሚነቅፉት ነገር ባለመሆኑ ነው:: ምክንያቱም አንደኛ አርአያን መለወጥ ከሚለው ምሥጢር ከመነሣት ካልሆነ በቀር «ሱሪ» በመሆኑ ብቻ «ሱሪ» መልበስን ለመንቀፍ በቂ መጽሐፍ ቅዱሳዊ መሠረት አይኖረንም:: ሁለተኛ ሁሉም ባይሆኑ አንዳንድ ሴቶች ሱሪ የሚለብሱበት የጤና መታወክን ጨምሮ አፍን የሚያሲዝ በቂ ምክንያት አላቸው:: ሦስተኛ ደግሞ መሠረት በሌለው ነገር ለመተቸት መሞከር የሚጎዳው የሚለብሱትን ሳይሆን ሐሜተኞቹንና እንተቻለን ባዮቹን በመሆኑ ነው::

## ስለ መጋጌጫ ነገሮች ምን ይባላል?

ሰዎች ልብስ የሚለብሱት በዋናነት ሰውነታቸውን ለመሸፈን ቢሆንም በሌላ ዘንድ አምሮ ለመታየት መርጦ መልበስም ብዙ ዘመን ተቆጥሮአታል:: የጥንት ዕብራውያን የሚጠቀሙትን ሁሉ ለመማረክ

አዘወትረው ሽቶ ይቀቡ፣ ቅባቶችንና መኳኳያዎችን ይጠቀሙ እንደ ነበር መጽሐፍ ቅዱስ ይመሰክራል::

ሆኖም በእግዚአብሔር ፊት ሞገስ የሚያመጣላቸውን ነገር ማድረግ የሚፈልጉ ወጣት ሴቶች ዋና ጌጣቸው «በእግዚአብሔር ፊት ዋጋው እጅግ የከበረ የዋህና ዝግተኛ መንፈስ» መሆን አለበት:: በተጨማሪም ምንም ነገር ቢሆን በልክና እጅግ ባልተጋነነ መልኩ መሆን እንዳለበት አለመዘንጋት ይጠቅማል:: ቅዱስ ጳውሎስ «ነገርን ሁሉ በልክ» እንድናደርግ መክሮናል:: 2ጢሞ4:5

ሌላው ወጣት ሴቶች ሁሉ ማወቅ ያለባቸው ከጥቅማቸው ይልቅ ጉዳታቸው እንደሚያመዝን ነው:: መዋቢያ ቅባቶች ጥሩውን ደም ግባት ሊያበላሹ ወይም መልከ ጥፉነትን የባሰ መጥፎ ሊያደርጉት ይችላሉ:: በተጨማሪም መጋጌጫ ቅባቶች ከማሳመር በስተጀርባ የሚበልጠውን የተፈጥሮ የወጣትነትን የፊት ጥራት፣ ወዝንና ቁንጅናን የሚደብቅና የሚያበላሽ ጎጂ ጎን አላቸው::

ልጃገረዶች በመዋቢያ ቅባቶች ያለ ልክ መጠቀማቸው ወደ ደካማ ጎናቸው ትኩረትን ከመሳብ ያለፈ ጠቀሜታ የለውም:: በተጨማሪም እንዲህ ማድረጋቸው በአንድ በኩል በሌሎች ዘንድ በመጥፎ እንዲተረጎምባቸው ሲያደረግ በሌላ በኩል ደግሞ ከጊዜ በኋላ በውጫዊ መልካቸው ባስተዋወቁት ወይም ባሳዩት ርካሽ አምሳል ጠባያቸው እንዲቀረጽ ተፅዕኖ ሊያደርግባቸው ይችላል::

ኩል፣ ቅባት፣ የጥፍርና የፀጉር ቀለም፣ እንሶስላና የመሳሰሉትን ነገሮች በሚመለከት እንዲጠቀምባቸው በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የተጠቀሱ ነገሮች ባይኖሩም ጥሩ ጥሩ መመሪያዎች ግን ተሰጥተዋል:: ሌሎች ቅዱሳት አዋልድ መጻሕፍትም የሚሻለውን





መንገድ ሳይጠቁሙ አላለፉም:: ለምሳሌ፦ የመልክዓ ማርያም ደራሲ ድንግል ማርያምን ሲያወድሱ «ሰላም ለአጽፋረ እግርኪ ዘኢፈቀዳ ለሥርጋዌ ጥምዓታተ ኅምር ምድራዌ» ብለዋል:: ትርጓሜው «እንሶስላ መሞቅና ሌላ ምድራዊ ጌጥን ላልፈቀዱ የእግር ጥፍሮችሽ ሰላምታ ይገባል» ማለት ሲሆን ይህም አፍአዊ ጌጣጌጥን አለመሻት የሚያስመሰግን ቁጥብነትና ግብረ ገብነት በሆኑን ያስረዳል:: ስለዚህ ልጃገረዶች ይህን በተመለከተ ሚዛናዊ ሆኖ መገኘት ይኖርባቸዋል:: (መልክዐ ማርያም)

መጋጌጫን በተመለከተ ወላጆች ለልጆቻቸው ተጨማሪ መመሪያዎች የማወጣት ተገቢ የወላጅነት መብት አላቸው:: አንድ ቤት ባለቤቶችን ከሚወክለው በላይ ልጆች ወላጆችን ይወክላሉ:: በወላጆቻቸው ስም ይጠራሉና:: ስለዚህ ልጆች የሚሠሩት ሥራ በሙሉ አሳዳጊዎቻቸው ምን ዓይነት ሰብእና እንዳላቸው ሊናገር ይችላል:: ከሁሉም በላይ ግን ክርስቲያን ነን እስካሉ ድረስ በስሙ የተጠሩበትን ኢየሱስ ክርስቶስንም ይወክላሉ:: ስለሆነም ወጣቶች «አለባበሴና የሰውነቴ አቋም ከወላጆቼ ክብርና ማንነት ይልቁንም ከክርስቲያንነቴ ጋር ይስማማልን?» በማለት ራሳቸውን መጠየቅ አለባቸው:: አንድ ቤት ፈርሶና ተላልጦ ቢታይ ባለቤቱን እንደሚያስነቅፍ የክርስቲያኖች ሕይወት ቤተ ክርስቲያንንና ወላጆቻቸውን ሊያስነቅፍ ይችላል:: የሰንበት ትምህርት ቤት ወጣቶች አባል ለሆኑበት ሰንበት ትምህርት ቤት ደንብና ሥርዓት ተገዢ ቢሆኑና ባያምፁ እጅግ ተጠቃሚ ይሆናሉ:: አንዳንድ ሰንበት ትምህርት ቤቶች ስለ አለባበስና ስለመሳሰሉት ሥነ ምግባራት ደንብ እንዳላቸው የታወቀ ነው::

## ስለ «መልክ» ሊኖር የሚገባ ተገቢ አመለካከት!

በኮረዳነት ወቅት የሚከሠቱ አካላዊ ለውጦች የስሜት ለውጦችን ሊያስከትሉ ይችላል:: አንዲት ልጃገረድ አንድ ጊዜ በኃይልና በብርታት የተሞላች ጤናማ ወጣት የሆነች ይመስላትና በሌላ ቅጽበት ደግሞ ድክምክም ብላ ፍጹም ጤና እንደሌላት እንደሚሰማት ሁሉ ስለማንኛውም ነገር የሚሰማት ስሜትም በዚያው ልክ በጣም ተለዋዋጭ ሊሆንባት ይችላል:: ከዚህ የተነሣ ብዙ ብሩህና የደስታ ወቅቶች በትካዜና በተስፋ መቁረጥ ተሞልተው ይታያል:: አሁን የወደደችውን ከጥቂት ደቂቃ በኋላ ያለ ምንም ተጠቃሽ ምክንያት መስልቸትና መጥላት ትጀምራለች:: በዚህ ምክንያት የወሰነቻቸው ውሳኔዎችና የወሰደቻቸው እርምጃዎች የማይሽር ጸጸት ሊያስከትሉባት ይችላሉ::

በዚህ ተለዋዋጭ ስሜት ላይ ነገሮች በሙሉ በሽግኔ መወርወሪያ ፍጥነት የሚቀያየሩበት ዘመናዊው የኢንዱስትሪ ዓለም ሲጨመርበት ወጣት ልጃገረዶችን ለከፍተኛ ጭንቀትና ግራ መጋባት ሊዳርጓቸው ይችላሉ:: በእርግጥ ጤናማ መሆኗንና ወደፊት ምን ዓይነት ሰው እንደሚወጣት ሊያሳስባት ይችላል:: በዚህ ያለመረጋጋት ሁኔታ በቀላሉ ላለመሸነፍ ብዙ ብቸኛና ዝምተኛ ወይም በጣም ትምክህተኛና እኔ ያልኩት ብቻ ይሁን ማለት አያዋጧትም::

ወጣት ልጃገረዶች ስለመልካቸው መሳሳትና መጨነቃቸው ከዘመነ ሔዋን ጀምሮ እንደ ነበር በመጻሕፍት ተገልጧል:: ይሁን እንጂ የሴቶች ጠቅላላ የወደፊት ሕይወት በመልክ ላይ የተመረኮዘ ይመስል ስለ ፊትና ቁመና ከመጠን በላይ መጨነቅ አይገባም:: በዙሪያሽ የሚገኙና በብዙ መንገድ የምትቀኚባቸውን ታላላቅ ሰዎች





አስተውለሽ ተመልክቻቸው:: አብዛኞቹ ተራ መልክ ያላቸው አይደሉምን? ስለዚህ ወደፊት ለሚኖርሽ ደስተኛ ኑሮ እውነተኛ ቁልፉ የቁመና ማራኪነት አለመሆኑን ለምን አታስተውዪም?

አካላዊ ውበትን የተላበስሽ ልጃገረድም ብትሆኚም ሐቁ ከዚህ አይዘልም:: ብዙ ቆንጆ ሴቶች በጣም ከንቱና ይልቁኑም የብልግና ኑሮ የሚኖሩ ሆነው እንደቀሩ መገንዘብ ይኖርብሻል:: ይህ ኑሮ ኀዘንና «ምነው ባልተፈጠርኩ?» የሚያሰኝ ጸጸት የሞላበት እንደሆነ ግልጽ ነው:: መልከ ጥፉ ሴት ከሆንሽ ብታስተውዪው ብዙ ቆንጆ ሴቶች ሕይወታቸው መና የቀረበት ፈተና ላንቺ እንደቀረልሽ ትረጃለሽ::

ውስጣዊ ማንነት እንጂ ውጫዊ ቁመና ከንቱና ጠፊ መሆኑን ማወቅ ካቃተሽ ምንም ቆንጆ ብትሆኚ ትልቅ ጥበብ ጎሎሻል ማለት ነው:: በዓለም አስቀያሚ ፍጥረት የሚባለው ደግሞ ጥበብ የጎደለው ነው:: መጽሐፍ ቅዱስ «የወርቅ ቀለበት በእሪያ አፍንጫ እንደሆነ ከጥበብ የተለየች ቆንጆ ሴትም እንዲሁ ናት» ይላል:: ምሳሌ 11፥22 በተጨማሪም «ውበት ሐሰት ነው፥ ደም ግባትም ከንቱ ነው፤ እግዚአብሔርን የምትፈራ ሴት ግን እርሷ ትመሰገናለች» የሚል ቃል ይገኛል:: ምሳ31፥30 አንቺ ምን ያህል እግዚአብሔርን ትፈሪዋለሽ? በዖታሽና በቁመናሽ ምን ያህል ደስተኛ ነሽ? ያለሽን ሕዋሳት በሙሉ እግዚአብሔር ባሉበት ሁኔታ ዐውቆ እንደሰጠሽ አስበሽ በደስታ ተቀብለሻል? እንዲህ ከሆነ በጣም ቆንጆ ሴት ነሽ ማለት ነዋ!

ተከሻ እየኖሩ እንክብካቤ የሚደረግላቸውና «የሚጦሩ» ናቸው:: ስለዚህ እነዚህ ወጣቶች ከብዙ ኃላፊነት ነጻ መሆናቸውን ዐውቀው ዕድላቸውን ቢጠቀሙበት ለመማርና ዕውቀት ለመሰብሰብ ሰፊ ጊዜ ይኖራቸዋል:: ሆኖም አብዛኞቹ ወጣቶች ያን ያህል ሰፊ ጊዜ እንደነበራቸው የሚያስተውሉት ጊዜው ካለፈ በኋላና ለመጠቀም የማይችሉበት ሁኔታ ውስጥ ሲገኙ መሆኑ እጅግ ያስቆጫቸዋል::

ትምህርት ትግልን ይጠይቃል:: መታገሉን ብትሰለች ከትግሉ በኋላ የምታገኘውን ዘለቄታዊ ጥቅም ታጣለህ:: ስለዚህ ወጣት ከሆንክ ኋላ የምትቆጭበትና ከሰው የምታንስበት ጫወታና መዝናናት አታሎኽ ከመማር አትቦዝን:: ለጊዜያዊ ደስታ ብለህ ዘለቄታዊ ጥቅምን ለምን ታጣለህ? መዝናናትና መደሰት ድሮም ነበሩ፤ የሚያልቁ ነገሮች አይደሉምና ወደፊትም ይኖራሉ:: ስለዚህ በሌላ ጊዜ የምትደርስባቸው እነዚህ ነገሮች እንዳያዘናጉህ ተጠንቀቅ:: የወደፊት የሥጋህና የነፍስህ ዕጣ ምን ሊሆን እንደሚችል ከወዲሁ በጥንቃቄ አስብበት:: ነቢዩ ኢሳይያስ «ወይስ ወሬ ማስተዋልን ለማን ይሰጣል?» ብሏልና ከወሬነት ለማያልፉ ነገሮች እየጓጓህ ትምህርትን ቸል አትበል:: ኢሳ28÷9

ጠቢቡ ሰሎሞን ታካች ሰው ብትልከው «አንበሳ በመንገድ አለ» ይላል በማለት እንደተናገረው ላለ መማር ምክንያት አታብዛ:: ምክንያት የሚያልቅ ነገር አይደለም:: ለምንም ነገር ምክንያት ሊቀርብ ይችላል:: ከዚያ ይልቅ ለሰው የሚያዋጣው ምክንያትን በብርታት አሸንፎ ጠንክሮ መማር ነው:: ብፁዕ አቡነ ዮሐንስ ቀዳማዊ አንዱን ወጣት ያለ ሥራ ስላዩት «ልጄ ለምን አትማርም?» ቢሉት እርሱም «አባታችን:- ምን በልቼ?» በማለት መለሰላቸው:: ብፁዕነታቸውም





ምክንያተኝነት እንደማይጠቅም በሚያስረዳ ቃል «ታዲያ አሁን እየደነቆርህ ያለኸው ምን እየበላህ ነው?» በማለት መለሱለት ይባላል::

ላለመማር የትምህርት ፖሊሲን፣ መምህራንን፣ ወላጆችን (ቤተሰብን)፣ ጾታን፣ የሥራ ጫናን፣ የጤና ሁኔታንና የመሳሰሉትን መከኑን ለማንም አልጠቀመም:: የተሻለው መንገድ በራስ በኩል ያሉትን ድክመቶች አስወግዶ ተገቢውን ጥረት ማድረግ ብቻ ነው:: ጥሮ በመማር መጠቀም እንጂ ቁጭ ብሎ ሌላውን ማማትና መተቸት ዐዋቂነት አይደለም:: ስለዚህ በቻልከው ሁሉ ጠንክረህ ተማር ከዐቅምህ በላይ የሆነውን ደግሞ ፈቃዱን አታውቅምና ለፈጣሪህ ተወው::

እንኳን ከጨዋታና ከመዝናናት ይቅርና ከሥራም ቢሆን መቅደም ያለበት ትምህርት ነው:: ዕውቀት ያልደገፈው ሥራ መሠረት እንደሌለው ቤት ነውና:: ሥራ ያለህም ሰው ብትሆን የየዕለት መሠረታዊ ፍጆታህን ካገኘህ በኋላ ሐሳብህ ወደ ትምህርት ይሁን:: ከተግባረ ሥጋም ሆነ ከተግባረ ነፍስ መቅደም ያለበት መማር ነውና::

በራስ አነሣሽነት ከትምህርት ይልቅ ዋዛ ፈዛዛንና በልምድ የሚገኝ ዕለታዊ ተግባርን የመረጠ ሰው የኋላ ኋላ የሚያዝንበትና የሚያፍርበት ነገር ሳያጋጥመው አይቀርም:: ጠቢቡ ሰሎሞን ትምህርትን በልዩ ልዩ ምክንያት ሳይማር የቀረ ሰው ዘግየት ብሎ የሚሰማውን ስሜት እንዲህ በማለት ይገልጸዋል:- «በመጨረሻም ሥጋህና ሰውነትህ በጠፉ ጊዜ ታለቅሳለህ፥ ትላለህም፥ እንዴት ትምህርትን ጠላሁ ልቤም ዘለፋን ናቀ! የአስተማሪዎቼንም ቃል አልሰማሁም፥ ጆሮቼንም ወደ አስተማሪዎቼ አላዘነበልሁም::» ምሳ5፡11-13

ይልቁንም ለመማር የሚያስችል ሁኔታ ተመቻችቶ ሳለ ለመሥራትና ንብረት ለማካበት መሽቀዳደም የከበረች ጥበብን ዋጋ ማሳጣት ነው:: ከገንዘብ ተግሣጽ ይበልጣልና:: ተግሣጽ ደግሞ ጥበብም ትምህርትም ነው:: ስለዚህ መጽሐፍ ቅዱስ «ተግሣጼን እንጂ ብርን አትቀበሉ:: ከምዝምዝ ወርቅም ይልቅ ዕውቀትን ተቀበሉ፣ ጥበብ ከቀይ ዕንቁ ትበልጣለችና የከበረ ነገር ሁሉ አይተካከላትም::» ምሳ8፥10-11 በማለት ትምህርት በገንዘብ እንደማይለካ ምስክርነቱን ይሰጣል:: ሲራ6፥18-37

## የትምህርት ዓይነቶች

ሐዋርያው ቅዱስ ያዕቆብ ምድራዊና ሰማያዊ፣ ሥጋዊና መንፈሳዊ በማለት ጥበብን በሁለት በመክፈል ጽፏል:: ስለምድራዊ ጥበብ ሲናገር፡- «ይህ ጥበብ ከላይ የሚወርድ አይደለም፣ ነገር ግን የምድር ነው፥ የሥጋም ነው» በማለት ሲገልጸው ሰማያዊውን ጥበብ ደግሞ «ላይኛይቱ ጥበብ ግን በመጀመሪያ ንጽሕት ናት፥ በኋላም ታራቂ፣ ገር፣ እሺ ባይ፥ ምሕረትና በጎ ፍሬ የሞላባት፥ ጥርጥርና ግብዝነት የሌለባት ናት::» በማለት ይገልጻታል:: ያዕ3፥15(17) ጥበብ ለሁለት ወገን ተከፈለች ማለት ትምህርትም ለሁለት ይከፈላል:: ምክንያቱም ጥበብ የሚገኝ ከትምህርት ነውና::

ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ደግሞ ትምህርትን ትምህርተ ክርስቶስና ትምህርተ ሰብእ (የሰው ትምህርት) በማለት ለሁለት ከፍሎ አስረድቷል:: ይህም «እንደ ክርስቶስ ትምህርት ሳይሆን፣ እንደ ሰው ወግና እንደ ዓላማዊ እንደ መጀመሪያ ትምህርት ባለ በፍልስፍና በከንቱም መታለል ማንም እንዳያማርካችሁ ተጠበቁ::» ባለው ይታወቃል:: ቆላ2፥8





ስለዚህ መንፈሳዊውን ትምህርት የክርስቶስ ትምህርት፣ መንፈሳዊ፣ የቤተክህነት፣ ሰማያዊ፣ ጥንታዊ በማለት ስንጠራው ዘመናዊውን ትምህርት ደግሞ ዓለማዊ፣ ምድራዊ፣ሰብአዊ፣ ወግ፣ ፍልስፍና፣ ሥጋዊ ትምህርት በማለት ልንጠራው እንችላለን::

ከቤተ ክርስቲያን የጸሎት መጻሕፍት መካከል አንዱ የሆነው መስተብቁዕ መንፈሳዊውን ትምህርት «የመለኮት ትምህርት» በማለት ይጠራዋል:: «ወሲሲ ልበነ በመለኮተ ትምህርት ወበለብዎ ዘእምነቢከ» ፍቺውም «በመለኮት ትምህርት ልቡናችንን መግብ፣ ከአንተ ዘንድ የሚገኘውንም ማስተዋል» ማለት ነው:: (መስተብቁዕ በእንተ ዝናማት)

በአሁኑ ጊዜ ሥጋዊውን ትምህርት በሀገራችን ለማዳረስ ኃላፊነት የተሰጠው ክፍል በሚኒስቴሮች መሥሪያ ቤት የትምህርት ሚኒስቴር ሲሆን እውነተኛውን መንፈሳዊ ትምህርት ለዓለም እንድታዳርስ ከጌታችን ከመድኃኒታችን ከኢየሱስ ክርስቶስ ሙሉ ኃላፊነትና ትዕዛዝ የተቀበለች ቤተ ክርስቲያን ናት:: ይሁን እንጂ ቤተ ክርስቲያን በሀገራችን ለመንፈሳዊውም ሆነ ለሥጋዊው ትምህርት መሠረት እንደ መሆኗ መጠን ዘመናዊውንም ትምህርት በሀገራችን ከማስፋፋት የቦዘነችበት ጊዜ የለም::

በሀገራችን በኢትዮጵያ ዘመናዊ ትምህርት በማይታወቅበት ጊዜ እንኳን ቤተክርስቲያን መንፈሳዊ ትምህርቷን በአስደናቂ መልኩ ቀርጻ ከፍልስፍና (ከዘመናዊ ጥበብ) ጋር ጐን ለጐን ስታስተምር ቆይታለች:: ከዚህም በተጨማሪ ለሀገርና ለሕዝብ መኩሪያ የሆነ ብቁ ፊደል ቀርጻ ማስረከቧ ሳያንሳት የፊደላቱን ምሥጢር፣ መልክና ቅርጽ በማስለየት እስከዛሬ ድረስ ግንባር ቀደም ሚና እየተጫወተች ነው:: ይህን ሁሉ

የመረመረ ሰው ቤተ ክርስቲያን ለመንፈሳዊ ትምህርት ብቻ ሳይሆን ለሥጋዊ ትምህርት መሠረት መሆኗን ለማወቅ አይቸገርም።

ሕንፃ ከማነጽ፣ ፍትሕት ከመፍታት፣ ከማጥመቅ፣ ከመቀደስ ይልቅ ቀዳሚው የቤተ ክርስቲያን ተልዕኮ ማስተማር ነው። ማስተማርና ማሳመን ከሌለ እነዚህ ምሥጢራት በሙሉ ላላመነ ሰው የሚፈጸሙ አይደሉምና። እንዲያውም ቤተ ክርስቲያን የተመሠረተችው በትምህርተ ወንጌል ነው። «ሊቀ ማኅበር» የሚባል ኢየሱስ ክርስቶስ ሁለትም ሦስትም ሆነን በምንሰበሰብበት ጊዜ በመካከላችን ይገኛል። «ያዘዝኋችሁንም ሁሉ እንዲጠብቁ እያስተማራችኋቸው ደቀ መዛሙርት አድርጓቸው እነሆም እኔ እስከ ዓለም ፍጻሜ ድረስ ሁል ጊዜ ከእናንተ ጋር ነኝ።» ማቴ28፥20፤18፥20 በማለት ከቃል ኪዳን ጋራ ቤተ ክርስቲያን በትምህርተ ወንጌል እንድትመሠረት የፈቀደ ራሱ ነውና።

ስለዚህ ቤተ ክርስቲያን ማስተማር የዘወትር ሥራዋ ነው። ትምህርቷም የሕይወት ትምህርት ነው። ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ «እናት አባት ልጆቻቸውን የእነርሱ ለማድረግ ቢፈልጉ ለቤተ ክርስቲያን ይስጡ። ከደግ በቀር ክፉ ነገር አታስተምራቸውምና።» በማለት የቤተ ክርስቲያን ትምህርት ለልጆች ያለውን ጠቀሜታ አስረድቷል።

የትምህርተ ወንጌልን አገልግሎት ቸል በማለት ለሌሎች መንፈሳዊ አገልግሎቶች ቅድሚያ የሚሰጡ የቤተ ክርስቲያን አካላት ቢኖሩ ዋናውን ጉዳይ ቸል ስላሉ ከዚህ ቀጥሎ ባለው የወንጌል ቃል ይገሠጻሉ። «በሕግ ያለውን ዋና ነገር ስለምትተዉ፥ ወዮላችሁ፤ ሌላውን ሳትተዉ ይህንን ልታደርጉ ይገባችሁ ነበር። እናንተ ዕውሮች መሪዎች፤ ትንኝን የምታጠሩ ግመልንም የምትውጡ።» ማቴ23፥23-





24 ዋናው የቤተ ክርስቲያን ተልዕኮ መንፈሳዊ ትምህርት ማስተማር ነውና።

ከቤተ ክርስቲያን ባሻገር ወላጆች ልጆቻቸውን «በተግሣጽና በምክር» የማሳደግ ኃላፊነት አለባቸው። ኤፌ6፥4 ሠለስቱ ምዕትም በሃይማኖተ አበው «ለልጆችህ አርምሞንና ጸጥታን አስተምራቸው፤ ሰነፍ አትሁን።» በማለት ወላጆችን መክረዋል። ልጆቻቸውን የማያስተምሩ ወላጆች ቅጣት እንደሚገባቸው ቅዱስ ባስልዮስ «ልጆችን መልካም ትምህርት ከማስተማር ቸል የሚሉ ወላጆች በሌላ በኩል ለልጆቻቸው ደግ ቢሆኑ በዚህ ብቻ ሊቀጡ ያስፈልጋቸዋል» በማለት ተናግሯል።

አስቀድሞ እንደተገለጸው ሥጋዊና መንፈሳዊ ጥበባት በምድራችን ይገኛሉ። ሁለቱም በአቀራረባቸው፣ በዓላማቸውና በሚሰጡት ጠቀሜታ እጅግ ይለያያሉ። አንዳንድ ጊዜ የሚስማሙበት የጋራ ነጥብ ሲኖራቸው ብዙ ጊዜ ደግሞ እጅግ የሚቃረኑበት ቦታ አለ። ታዲያ ሰው አስቀድሞ መማር የሚኖርበት የትኛውን ትምህርት ነው?

## የትኛው ይቅደም?

በዚህ ዘመን ለሚከሠቱ ልዩ ልዩ ወንጀሎች መበራከት መንሥኤው የዕውቀት ማነስ ሳይሆን የግብረ ገብነት መጉደል ነው። ይህንን ችግር በመጠኑም ቢሆን መንግሥት የተረዳው ይመስላል። ምክንያቱም እንደ ድሮው ሁሉ ዛሬም በየትምህርት ቤቱ የሥነ ዜጋ ትምህርት (ሲቪክ ኤጁኬሽን) እና የሥነ ምግባር ትምህርት መስጠት ተጀምሯል። ይህም ቢሆን እግዚአብሔርን መፍራት አያሳድርምና ብቻውን ዓላማውን ሊመታ አይችልም።

ሰው ሁሉ የመልካም ሥነ ምግባር ባለቤት እንዲሆን በመጀመሪያ እግዚአብሔርን መፍራት ይኖርበታል:: እግዚአብሔርን መፍራት የሚገኘው ደግሞ ከመንፈሳዊ ትምህርት ነው:: ቅዱስ ዳዊት «ልጆቼ ኑ ስሙኝ እግዚአብሔርን መፍራት አስተምራችኋለሁ» መዝ33፥11 በማለት የተናገረው ቃል ለዚህ ምስክር ነው:: «ከእሾህ ወይን ከኩርንችትም በለስ» እንደማይለቀም ሁሉ ሰው ሁሉ እግዚአብሔርን እንዲፈራ ለማድረግ ዓላማ ይዞ ያልተቀረጸ ትምህርት ሁሉ እግዚአብሔርን ስለመፍራት ሊያስተምር አይችልም:: ስለዚህ በጥሩ ሥነ ምግባር ተኮትኩቶ ለማደግ አስቀድሞ መንፈሳዊ ትምህርትን መማር ይገባል:: «የጥበብ መጀመሪያ እግዚአብሔርን መፍራት ነውና» ምሳ1፥7፤ መዝ110፥10

መንፈሳዊ ትምህርት እንደ ራት ሲሆን ሥጋዊ ትምህርት ግን እንደ ዳረጎት ነው:: ከእራትና ከዳረጎት ዳረጎትን የሚመርጥ ማንም የለም:: ዳረጎት እራት አይሆንምና:: እንደዚሁም ሁሉ ጊዜያዊ እንጂ ዘለዓለማዊ ጥቅም የሌላት ሥጋዊ ጥበብ ከመንፈሳዊ ጥበብ መቅደም የለባትም:: ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ማንኛውም ሰው በሕይወት ዘመኑ ማስቀደም ያለበት ወደ እግዚአብሔር መንግሥት ለመግባት የሚረዳውን ነገር መሆን እንዳለበት ሲገልጽ «አስቀድማችሁ የእግዚአብሔርን መንግሥት ጽድቁንም ፈልጉ ይህም ሁሉ ይጨመርላችኋል» በማለት ተናግሯል:: ማቴ6፥33

ሠለስቱ ምዕት ልጆችና ወጣቶች አስቀድመው ምን መማር እንዳለባቸው በትእዛዝ መልክ እንዲህ ብለዋል:- «ቅድመ መሀርዎሙ ለውሉድክሙ መጽሐፈ ሲራክ ወሰሎሞን ወመዝሙረ ዳዊት» ይህም «አስቀድማችሁ ለልጆቻችሁ የሲራክን የሰሎሞንን መጻሕፍትና የዳዊትን መዝሙር አስተምሯቸው» ማለት ነው:: ይልቁንም





«አስቀድማችሁ» እና «አስተምሯቸው» የሚሉት ቃላት ልጆች ከዘመናዊ ትምህርት አስቀድመው መንፈሳዊውን ትምህርት እንዲማሩ የማድረግ ኃላፊነት የወደቀው በወላጆች ላይ መሆኑን ይጠቁማሉ::

ይህ የአበው ትዕዛዝ መንፈሳዊው ትምህርት ከሥጋዊው ትምህርት መቅደም እንዳለበት ብቻ ሳይሆን ከመንፈሳዊ መጻሕፍትም ለወጣቶች ከላይ የተጠቀሱት መጻሕፍት መቅደም እንዳለባቸው ያስረዳል:: ምክንያቱም እነዚህ መጻሕፍት ወጣቶች በአእምሮ የበሰሉ እንዲሆኑ ከማድረጋቸውም በላይ ሥጋዊውንና መንፈሳዊውን ጥበብ አጣምረው ለመረዳት እንዲችሉ ያደርጓቸዋል::

ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ለሃይማኖት ልጁ ለጢሞቴዎስ በላከው መልእክቱ «ማንም ባልቴት ግን ልጆች ወይም የልጅ ልጆች ቢኖሩአት፥ እነርሱ አስቀድመው ለገዛ ቤተሰቦቻቸው እግዚአብሔርን መምሰል ያሳዩ ዘንድ ለወላጆቻቸውም ብድራትን ይመልሱላቸው ዘንድ ይማሩ» በማለት ልጆችና ወጣቶች አስቀድመው ምን መማር እንዳለባቸው በግልጽ ተናግሯል:: መማር ያለባቸውም ተገልጦ ሊታይ የሚችል «እግዚአብሔርን መምሰል» እና ወላጆቻቸውን በመጦር መንከባከብ ማለትም «ብድራትን መመለስ» መሆን እንደሚገባው አስረድቷል::ወላጆችን መርዳትና እግዚአብሔርን መምሰል የሚገኝበት ትምህርት መንፈሳዊ ትምህርት መሆኑ ግልጽ ነው:: ይህን ተረድቶ መንፈሳዊውን ትምህርት አስቀድሞ መማር ምን ያህል እግዚአብሔርን እንደሚያስደስተው «ይህ በእግዚአብሔር ፊት መልካምና የተወደደ ነውና» በማለት ጨምሮ ገልጧል:: 1ጢሞ5፥4

አንድ ክፉ ሰው ከተጻናወተህ በኋላ ምንም እንኳን ጉጂነቱን በበቂ ሁኔታ ብታውቅ ካንተ ለማራቅ እጅግ ይቸግርሃል:: እንደዚሁም ሁሉ ዓለማዊ ትምህርትን አስቀድመህ ተምረህ ከሃይማኖትህ ጋር

የሚጣረሱትን ጽንሰ ሐሳቦች ከተለማመድካቸው በኋላ እነዚህን አስወግደህ ሃይማኖተኛ ለመሆን መቸገርህ አይቀርም:: ዘመናዊ ትምህርት ለማመን ዳተኛ ያደርጋል፣ የሕሊና ሙግት ይፈጥራል፣ ጥያቄ እንድታበዛ ያደርጋል፤ ከማመን ይልቅ እንድትመራመር ይገፋፋሃል:: እነዚህ ነገሮች ደግሞ በመንፈሳዊ እይታ መጠነኛ ጥቅም ሲኖራቸው የሚያመዝነው ግን ጉዳታቸው ነው:: እንኳን ዘመናዊ አስተሳሰብና ትምህርት ወደ ውስጥህ ቀድሞ ገብቶ ይቅርና ትምህርተ ሃይማኖትን አስቀድመህ ከተማርክ በኋላ እንኳን ዘመናዊውን ትምህርት ስትማረው በመንፈሳዊነትህ ላይ ከፍተኛ ተፅዕኖ ያሳድርብሃል:: ለዚህ ምስክር የሚሆኑ በመጀመሪያ በሃይማኖት ትምህርት ከተደላደሉ በኋላ በዘመናዊ ትምህርት መርሕና አስተሳሰብ ተውጠው ሃይማኖተኛ እንደነበሩ ይቅርና ስለሃይማኖት ሰምተው እንኳን ማወቃቸው የሚያጠራጥሩ በርካታ ሰዎች በዙሪያህ ይገኛሉ:: ስለዚህ ከምንም በላይ የሚጠቅመው ትምህርተ ሃይማኖትን አስቀድሞ መማር ነው::

## በሚገባ መማር

ትምህርትን ሲከታተሉ በፍቅርና በሙሉ ኃይል ጥረት ከማድረግ ጋር ከሆነ ውጤቱ ያማረ ይሆናል:: ብዙ ወጣቶች ለትምህርት የተነሣሣ ልብ ስለሌላቸው በሚገባ አይማሩም:: በትምህርት ገበታቸው ላይ እንኳን የሚገኙት ሌላ ምክንያት ሲኖራቸው ወይም ደስ ሲላቸው ብቻ ነው:: ማጥናቱንም ቢሆን የሚያከናውኑት ፈተና ለማለፍ ያህል ነው:: ይህም ሊሆን የሚችለው በጣም ተግተዋል ከተባለ ነው:: አንተስ የምታጠናው እንዴት ነው? ስልቹ ሰው የቆረሰውን እንጀራ ለመጉረስም ይታክታልና:: ስልቹ ሰው አትሁን! ደግሞም «መልካም ሥራን ለመሥራት አንታክት» ገላ6፥9፡





2ተሰ3፥13 የሚለውን የእግዚአብሔር ቃል እንደ ስንቅ ብትይዘው ከመሰልቸት ያድንኃል::

በምንም ምክንያት በሚያስተምርህ መምህር ጥላቻ እንዳያድርብህ ተጠንቀቅ:: ይህ በትምህርትህ ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ አለውና:: ከመምህራን ጋር በፍቅር ለመኖር የምታደርገው ጥረት ባይሳካልህ እንኳን ተግቶ ከመማር ግን ተስፋ ሊያስቆርጥህ አይገባም:: እንደ ምንም ተቸግረህና ለፍተህ ተማር! ጊዜ ጠብቆ የለፋበትን መስጠት የእግዚአብሔር ድርሻ ነውና ተግተህ መማርህን እንጂ ውጤትህን አታሰላስል::

በሚገባ ብትማር ዕውቀት ካንተ ጋር ትሆናለች፣ ስትሰንፍ ደግሞ ትለይሃለች:: ከጉብዝ ተማሪ እየቀዳህ (እየኮረጅህ) ለማለፍ አትሞክር:: ይህ ለዘለቄታው የሚጠቅም አይደለምና:: በዚህ ሁኔታ ካሰብክበት ለመድረስ አትችልም:: ብትደርስም እንኳን የሚሰጥህን ኃላፊነት በብቃት መወጣት አትችልም:: በራስ የመተማመን ስሜትህ ይጠፋል:: ደግሞም በኩረጃ ማለፍ ሁልጊዜ የሚሳካ ነገር አይደለም፡ ቢሳካም እንኳን ሌብነትንና ኃጢአትን መለማመድ ነው:: ደግሞስ ራስህን ጉብዝ ማድረግ ካላወቅህበት ወደፊት ለሚያጋጥሙህ የሕይወት ጥያቄዎች ማን ሊያስኮርጅህ ይችላል? ለዚህ ችግር መፍትሔው ራስን ጉበዝ ማድረግ ብቻ ነውና ጠንክሮ መማር ይኖርብሃል::

በመደበኛ ክፍለ ጊዜ የምትከታተለውን ትምህርት በሚገባ ካልተወጣኸው በኋላ ለመማር ቁጭት ቢያድርብህ እንኳን ብዙ እንቅልፋቶች ያጋጥሙሃል:: በመጀመሪያ የምትፈልጋቸው ሥልጠናዎች አንተ ባለህ ውጤት በቀላሉ ላይገኙ ይችላሉ:: ቢገኙም ብዙ ገንዘብ የሚያስወጡህ ሆነው ነው:: ታዲያ መደበኛ ተማሪ እያለህ

በሚገባ በመማር ዕድልህን ለምን አትጠቀምበትም? ተግተህ በመማርህ የምትጠቀመው አንተ ራስህ ነህ:: «ሰው የሚዘራውን ሁሉ ያንኑ ደግሞ ያጭዳልና» የሚለው የመጽሐፍ ቅዱስ ቃል እንዲሁ የሚቀር አይደለምና:: ገላ6፥7

ዕውቀት የሚገነባው ሌሎች ሰዎችን መሠረት በማድረግ ነው:: ስለዚህ ከሌሎች ሰዎች ጋር ሳትነጋገር፣ የጻፉትን ሳታነብ፣ ወይም ትምህርትን ዓላማ አድርገህ ሲሠሩ ሳትከታተል ሌሎች ያገኙትን ዕውቀትና ልምድ ልትቀስም አትችልም:: ይህን ሁሉ ለማድረግ ደግሞ በቂ ጊዜ ያስፈልግሃል:: ማወቅ የሚገባህን ነገሮች ሳታውቅ ከተቃራኒ ጾታ ጋር ወዳጅነት ብትፈጥር ምን እንደሚያስከትልብህ ታውቃለህ? ዕውቀት ከምትገበይባቸው ሰዎችና ነገሮች ጋር ያለህ ግንኙነት እንዲጠብ ወይም እንዲቋረጥ በማድረግ ትኩረትህ ወደ አንድ ፆታዊ አቅጣጫ ብቻ እንዲሆን ያደርግና በዕውቀት እንዳታድግ ትሆናለህ:: ስለዚህ ይህን ከመሳሰለ አካሄድ ለጊዜው ብትቆጠብ እዕቀትን ከመራብ ትድናለህ:: ለሁሉም ጊዜ አለውና::

## የትምህርት ጥቅም

መማር የሚኖርብህ ልጅ በመሆንህ ተገደህ ወይም ምንም ምርጫ ስላጣህ መሆን የለበትም:: ትምህርት ብዙ ጥቅም እንዳለው ዐውቀህ ከልብ በመነጨ ፍላጐትና ጥረት ብትማር ለወደፊት ኑሮኽ ምን ዓይነት ባልንጀራ ማፍራት እንዳለብህ፣ ምን ብትሠራ እንደምትጠቀምና በሕይወትህ ዙሪያ ለሚፈጠሩ የሕሊና ጥያቄዎች በቀላሉ መልስ እንድታገኝ ጥሩ መሠረት ይጥልልሃል::





ትምህርት ሌሎች ሰዎች ከዚህ በፊት የሠሩትን ወይም አሁን በመሥራት ላይ ያሉትን ነገሮች ለማወቅ ያስችላል:: በሥራቸውም የተሳካላቸውንና ውድቀት ያስከተለባቸውን አካሄድ በመለየት በሙከራ ጊዜ ሳታጠፋና በእነርሱ ላይ የደረሰውም ውድቀት ሳይደርስብህ የትኛውን ጐዳና መከተል እንዳለብህ ለመወሰን ይረዳሃል::

ከልብ የተማረ ሰው ጊዜውን ጠብቆ መጠቀሙ አይቀርም:: የተማረውን ትምህርት ለሌሎች በማስተማር፣ የፈጠራ ሥራዎችን በመሥራት፣ ወይም ተምሮ ባገኘው ሙያ ምንደኛ ሆኖ በሚያገኘው ገቢ ራሱን ማስተዳደር ይችላል:: ከዚህም በተጨማሪ የሙያ ተሰጥኦቹን በመጠቀም ያለአግባብ የሚያወጣውን ወጪ መቀነስና ለራሱ የተመቻቸ ሁኔታን ሊፈጥር ይችላል:: ለምሳሌ:- የምግብ አዘጋጃጀት ትምህርትን የተከታተለ አንድ ሰው የሚፈልገውንና የሚስማማንው የምግብ ዓይነት በማዘጋጀት ጤናውን ለመጠበቅ ከመቻሉም በላይ መመገቢያ ቤቶችን (ሆቴሎችን) በመጠቀም የሚያወጣውን ያልተመጣጠነ ወጪ በመቀነስ ራሱን ለመርዳት ይችላል:: በተመሳሳይ ሁኔታ አንድ የቴክኒክ ሙያ ሥልጠና የወሰደ ሰው በዙሪያው ከሚገኙ ነገሮች በመጠቀምና ወጪ ሳያስፈልገው ልዩ ልዩ መገልገያዎችን ለራሱ ማበጀት ወይም የተበላሹ ንብረቶቹን ያለተጨማሪ ወጪ ራሱ ሊጠግናቸውና ሊያድሳቸው መቻሉም ከመማር የሚገኝ ጉልህ ጥቅም ተደርጐ ሊጠቀስ ይችላል::

አንድ ሰው የተማረውን ትምህርት በቀጥታ በሥራ ላይ ለማዋል በማይችልበት ሁኔታ ውስጥ ቢገኝ እንኳን ትምህርት አይጠቅምም ለማለት አይቻልም:: እንደዚህ ዓይነት ሰው ምንም እንኳን በተማረው ትምህርት በቀጥታ ገቢ አግኝቶ ተጠቃሚ ባይሆንም ትምህርቱ በሌላ አቅጣጫ ተጠቃሚ እንደሚያደርገው ማስተዋል ይገባል:: ምክንያቱም መማር ለመማር ከተዘጋጀንበት

መደበኛ ትምህርት ውጭ በሂደቱ ተዕግሥትን፣ ተጋትን፣ ሐሳብን ሰብስቦ የመከታተል ችሎታን፣ መጠየቅንና የማንበብ ልምድን እንድናዳብር ከማድረጉም በላይ አእምሮአችን እንዲሰፋ ያደርጋል:: የሠሩበት አካል እንደሚጠነክር ሁሉ የተማሩበትም አእምሮ መዳበሩ አይቀርም:: ይህም በዋጋ ሊተመን የማይችል የትምህርት ሁለ ገብ ጥቅም ነው::

## በትምህርት መኖር «ጥበቃ» ነው!

ቦዘኔ አእምሮ ብዙ ክፉ ሐሳቦችን ሲወልድ ይውላል:: «ሥራ ፈት አእምሮ የሰይጣን ቤተ ሙከራ ነው» መባሉ ተገቢ ነው:: ሰዎች ጊዜያቸውን ለመልካም ነገር ካልተጠቀሙበት ለክፉ ተግባር የሚያወሉት የተትረፈረፈ ጊዜ ይኖራቸዋል:: በመልካም ተግባር ወይም በመማር የተጠመዱ ከሆኑ ግን ክፉ ሐሳብ ቢፈጠርባቸው እንኳን ከጊዜ እጥረት የተነሣ ሳያከናውኑት ይቀራሉ::

ለብዙ ወጣቶች የሥነ ምግባር ጉድለቶች ተጠቃሽ የሚሆነው ቦዘንተኝነት ወይም ሥራ አጥነት ነው:: የእነዚህ ሰዎች አእምሮ በሥራ ባለመጠመዱ ምክንያት ወደ ልዩ ልዩ ክፉ ጉዳና ይተማል:: የአብዛኞቹ ሰካራሞች፣ የጫት ቃሚወች፣ የሲጃራ አጫሾች፣ የአደንዛዥ ዕፀዋትና መድኃኒት ሱሰኞች ሕይወት ቢፈተሽ ለሥራና ለትምህርት ግድ የለሾች መሆናቸውን መረዳት ይቻላል:: ይህ ማለት ግን ከሠራተኞችና ከምሁራን ይህን በመሰለ ርካሽ ተግባር የተመረዙ የሉም ማለት አይደለም::

አሳዛኝ ውጤቶችን በሚያስከትሉ በጾታ ብልግና፣ በአደንዛዥ ዕፅ ሱሰኝነት፣ በሌብነት፣ በቡድን ጸብና በመሳሰሉት ልዩ ልዩ የዓመፅ ተግባራት የተመረዙ ባልንጀሮችህን ጨምሮ በርካታ ሰዎች በዙሪያህ ይገኛሉ:: ይህን ከመሳሰሉት ሰዎች ጋር መዋል ቅር ሳያሰኝህ





አይቀርም:: ምንም እንኳን ከነዚህ ሰዎች ጋር ያለህን ግንኙነት በቀላሉ ለማስቀረት ያስቸግረህ ቢሆንም ትምህርትህን በሚገባ ብትከታተል ግን እንዲህ ካሉ መጥፎ ሰዎች ጋር ያለህን የጠበቀ ግንኙነት ቀስ በቀስ ለመቅረፍ ትችላለህ:: ለትምህርት ጥሩ ትኩረት በምትሰጥበት ጊዜ ሰፊ ጊዜህን ይይዝልሃል:: ይህም ሥነ ሥርዓት ከጐደላቸው ሰዎች ጋር የሚኖርህን ግንኙነት ውስን ያደርገዋል:: እንደዚህ ያሉ ሰዎች ፍላጐትህ ትምህርትህን በሚገባ መከታተል ብቻ መሆኑን ሲያዩ ከጊዜ በኋላ ሊተዉህ ይችላሉ:: ይህም ከትምህርት የምታገኘው «ጥበቃ» ነው::

መጽሐፈ መነከሳት የማንበብ ልምድና ትምህርት በንጽሕና ተጠብቆ ለመኖር አጋዥ መሆናቸውን እንዲህ ሲል ይገልጻል:- «ፃማ ሥጋዊት ወአንብቦ መጻሕፍት አሞላካውያት የዐቅብዋ ለንጽሕና» በአማርኛ «በሥጋ መድከምና አምላካዊያት መጻሕፍትን ማንበብ ንጽሕናን ይጠብቋታል» ማለት ነው:: (ማር.ይስ.አን.ሣልስ.ምዕ 9)

## የመንፈሳዊ ትምህርት ጥቅም

ያለንበት ዘመን ከየትኛውም ጊዜ ይልቅ የትምህርት ጥቅም ጐልቶ የሚታይበት ዘመን ሆኗል:: ከላይ በጥቂቱ የተገለጹት ዕሤቶች ከሥጋዊ ትምህርት የሚገኙ ናቸው:: ሥጋዊ ትምህርት እንደዚህ የሚጠቅም ከሆነ መንፈሳዊ ትምህርት ደግሞ እጅግ በተሻለ ሁኔታ እንደሚጠቅም ጥርጥር የለውም:: ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ማንኛ ውም ሥጋዊ ነገር ያለው ጠቀሜታ ከመንፈሳዊ ነገር ጠቀሜታ ጋር ሲነጻጸር እጅግ ጥቂት እንደ ሆነ እንዲህ በማለት ይገልጻል:: «ሰውነትን ለሥጋዊ ነገር ማስለመድ ለጥቂት ይጠቅማልና፣ እግዚአብሔርን መምሰል ግን የአሁንና የሚመጣው ሕይወት ተስፋ

ስላለው ለነገር ሁሉ ይጠቅማል::» 1ጢሞ4፥8 ስለዚህ መንፈሳዊ ትምህርት የሚሰጠው ጠቀሜታ ከሥጋዊ ትምህርት እጅግ የላቀ ነው:

በስሕተታቸው ጸንተው የሚኖሩ ሰዎች ሥራዬ ትክክል ነው ብለው የሚያምኑ ወይም መሳሳታቸውን በውል ያልተረዱ ናቸው:: ከዚህ ካለፈ ደግሞ ስሕተታቸውን ቢያውቁም ከዘለቄታዊ ጥቅም ይልቅ ለጊዜው የፍላጐታቸውን መሳካት የሚወዱ ከመሆን አይዘሉም:: ካለማወቅ የተነሣ የተሳሳቱ ሰዎች መላልሰው ሥራቸውን ቢመረምሩትና በቂ ግንዛቤ እስኪያገኙ ድረስ ስለ ሥራቸውም አስከፊነት ቢማሩ ከሕህተት ይታረማሉ:: መማር ከመሳሳት ያድናልና::

የማይሳሳት የለም፤ ከስሕተት ሁሉ የሚከፋው ግን በሃይማኖታችን ላይ የምንፈጥረው ስሕተት ነው:: ለምን ቢባል ጉዳቱ የነፍስ ስለሆነ ነው:: ከዚህም ዓይነት ስሕተት ቢሆን መዳን የሚቻለው በመማር ነው:: አለማወቅ ለሕህተት መንሥኤ ከሆነ መማርና ማወቅ ከስሕተት ለመዳን መፍትሔ መሆኑ ግድ ነው:: ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በትንሣኤ ላይ ባላቸው እምነት ችግር ለነበረባቸው ለሰዱቃውያን የስሕተታቸው መነሻ ምን እንደ ነበር ሲነግራቸው «መጻሕፍትንና የእግዚአብሔርን ኃይል አታውቁምና ትስታላችው» ብሏቸዋል:: ማቴ22፥29 ስለዚህ ትምህርት ካሉት ዋና ዋና ጥቅሞች መካከል «ከስሕተት ለመዳን» የሚለው በአንደኛነት ይጠቀሳል::

ከስሕተት ለመዳን ብቻ ሳይሆን ለማመንና እግዚአብሔርን ፈርቶ ለመኖርም ትምህርት ወሳኝ ነገር ነው:: ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ሳይማሩ ሃይማኖተኛ ሰው መሆን እጅግ አስቸጋሪ እንደ ሆነ «ባልሰሙትስ እንዴት ያምናሉ? ያለ ሰባኪስ እንዴት ይሰማሉ?»





በማለት ተናግሯል:: ሮሜ10፥14 ቅዱስ ዳዊት ደግሞ «ልጆቼ ሆይ ስሙኝ እግዚአብሔርን መፍራት አስተምሯችኋለሁ» መዝ33፥11 በማለት ማመን ከትምህርት እንደሚገኝ ተናግሯል:: በዓይን ያላዩትን እግዚአብሔርን መፍራት ማመን ይባላል::

ለማመን ብቻ ሳይሆን መልካም ሥራ ለመሥራትም መማር ያስፈልጋል:: የማያውቁትን መሥራት ስለሚያስቸግር ለመሥራት ማወቅ፣ ለማወቅ ደግሞ መማር ግድ ነው:: ማወቅ ለመሥራት ብቻ ሳይሆን በሥራችን የትክክለኛለነት ስሜት እንዲሰማንና ያለማቋረጥ በጉጉት እንድንሠራው ያግዘናል:: በአጠቃላይ በመንፈሳዊም ሆነ በሥጋዊ ጉዳና የሚሠሩ ሥራዎችን ለማከናወን መማር ያስፈልጋል:: ለዚህም ነቢዩ ኢሳይያስ «መልካም መሥራትን ተማሩ» በማለት የተናገረው ቃል በቂ ማስረጃ ነው:: ኢሳ1፥17፤ 26፥9-10

መንፈሳዊ ትምህርት ለበጎ ሥራ ያዘጋጃል:: «የእግዚአብሔር ሰው ፍጹምና ለበጎ ሥራ የተዘጋጀ ይሆን ዘንድ» በማለት ቅዱስ ጳውሎስ የተናገረው ቃል ከላይ የተጠቀሰውን ሐሳብ ይደግፋል:: 2ጢም3፥16 መንፈሳዊ ትምህርት ለበጎ ሥራ የሚያዘጋጅ፣ የሃይማኖት ሰው እንድንሆን የሚያደርግ በመሆኑ በነፍስም ሆነ በሥጋ እጅግ ጠቃሚ ነው:: የመንፈሳዊን ትምህርት ጥቅም በጭር ቃል ስናጠቃልለው «መዳን የሚገኝበት ጥበብ» እንለዋለን:: 2ጢሞ3፥15 ምክንያቱም ይህ ጥበብ ሰው የእምነትንና የምግባርን እርካብ እየረገጠ ወደ መንግሥተ ሰማያት ለመውጣት ስለሚያስችለው ነው::

ከዚህ ሁሉ በላይ ደግሞ መንፈሳዊ ትምህርት ወደ አእምሮ የሚገቡትን የዘመናዊ ትምህርት ፅንሰ ሐሳቦችንና ማንኛውም ዓይነት ዕውቀቶችን ምን ያህል እውነተኛና ጠቃሚ እንደሆኑ ለመመዘን ይረዳል:: መንፈሳዊ ትምህርት ከዘመናዊ ትምህርት መቅደም

የሚኖርበትም ስለዚህ ነው:: አንድ ሰው አስቀድሞ መንፈሳዊውን ትምህርት በሚገባ የተማረ ከሆነ ለወደፊት ሕይወቱ የሚበጀውንና ከእግዚአብሔር አንድነት እንዳይለይ የሚረዳውን ነገር ሁሉ ለይቶ ያውቃል::

«ሥራ» ተብለው ነገር ግን ከመንፈሳዊ ሕይወት ጋር ፍጹም የሚቃረኑ ብዙ መስኮች አሉ:: አንድ ክርስቲያን አስቀድሞ መንፈሳዊ ግንዛቤ ካለው ከፈጣሪ አንድነት የሚለዩትን እነዚህን ነገሮች እየተማረና እያጠና ገንዘቡንና ጊዜውን አያባክንም:: ለምሳሌ:- ቤተ ክርስቲያን ከመጽሐፍ ቅዱስ መረጃ በመጥቀስ «ዘፋኝነትን» ታወግዛለች:: አንድ ሰው ደግሞ ደግሞ መንፈሳዊነትን መላበስ እየፈለገና የቤተ ክርስቲያን ልጅ ሆኖ ሳለ አንድን የሙዚቃ መሣሪያ አጨዋወትና ጥሩ ዘፋኝ ለመሆን የሚያስችል የድምጽ አወጣጥ ጥበብን ቢያጠና በሕይወቱ ብዙ ነገሮች አይቃወሉበትም? ምክንያቱም ሌላ ሥራ እንዳይሠራ ገንዘቡንና ጊዜውን አቃጥሎ ያገኘው ሙያ ቢኖር የሙዚቃ መሣሪያ መጫወትና ዘፋኝነት ነው:: እንዳይተወው ደግሞ ምን ሠርቶ ይኑር? በዚሁ ሥራው ተሰማርቶ እንዳይኖር ደግሞ ከፈጣሪው ጋር ያለው ግን በእጅጉ ይበላሸበታል:: ለዚህ ሁሉ ችግር መፍትሔ የሚሆነው በምን መልኩ ብንጓዝ እንደምንጠቀም ከወዲሁ ለይተን እንድናውቅ የሚረዳንን መንፈሳዊ ትምህርት አስቀድመን ብንማር ነው::

ብዙ ክርስቲያኖች ጥሩ መንፈሳዊ ሰው መሆን ያልቻሉት ከላይ የተጠቀሰው ዓይነት ውስብስብ ችግር ስላጋጠማቸው እንጂ መሆን ሳይፈልጉ ቀርተው አይደለም:: እንዲህ ያለ ችግር ያጋጠማቸው ሰዎች ቀስ በቀስ ሥራቸውን በሌላ አማራጭ እየተኩ ከፈጣሪ ጋር ያላቸውን ዝምድና ከማጠናከር ውጭ ባሉበት ሁኔታ ጥሩ መንፈሳዊ ሰው መሆን የሚችሉበት ምንም ዓይነት መንገድ





የለም:: ከዚህ ሁሉ የሚከፋው ደግሞ «ካፈርኩ አይመልሰኝ» እንደሚባለው ሥራቸው በቅዱስ መጽሐፍ የተወገዘ ሆኖ ሳለ አንድ ጊዜ ስለገቡበት ብቻ ሥራቸውን መጽሐፍ ቅዱስ እንደማይቃወመው አድርገው ለማስረዳት የሚሞክሩ ሰዎች መኖራቸው ነው:: ተሳስቻለሁ! እኔ በሄድኩበት እንዳትሄዱ ብሎ ማስረዳት አንዱ መንፈሳዊነት ሆኖ ሳለ ሌሎችም ተጨምረው እንዲሳሳቱ «ሥራዬ ልክ ነው» ማለት «እኔ ከሞትኩ ሰርዶ አይብቀል» የሚል ዓይነት የምቀኝነት ሥራ ነው:: አንተ ወጣት የምትማረው ትምህርትና የወደፊት የሥራ መሰማሪያህ በመንፈሳዊ ሕይወት ለአንድ ክርስቲያን መኖር እስከሚገባው ድረስ ዘልቆ ከመሄድ የሚያግድህ እንዳይሆንብህ ትጠነቀቃለህ? ከሆነ ደህና ካልሆነ ግን ለነፍስህ ምንም እንዳላሰብክላት እወቅ:: ስለ ወደፊት መንፈሳዊ ማንነቱ ምንም የማያስብ ሰውስ እንዴት ክርስቲያን ሊባል ይችላል?

## ትምህርት ጉዳት ይኖረዋል?

ቅዱሳት መጻሕፍትና ትምህርቶቻቸው የተገኙት ከማይሳሳት ከእግዚአብሔር በመሆናቸው ፍጹምና እንከን የለሽ ናቸው:: ቅዱስ ዳዊትም «በምድር ላይ እንደ ተፈተነ ሰባት ጊዜ እንደ ተጣራ ብር የእግዚአብሔር ቃል የነጻ ቃል ነው::» በማለት የመንፈሳዊ መጻሕፍትን ፍጹምነት መስክሯል:: መዝ11፥6 በዚህ ምክንያት ቅዱሳት መጻሕፍትን ማሻሻል፣ በዙ ብሎ መቀነስና አንሰዋል በማለት ለመጨመር መሞከር ከባድ መንፈሳዊ ቅጣት ያስከትላል:: ራእ22፥18-19፤ ዘዳ4፥2

እነዚህን ቅዱሳት መጻሕፍት የሰው ልጅ በሚገባ ባለመማሩ ይጐዳል እንጂ እነርሱን በመማሩ የተነሣ የሚጐድልበትና የሚጐዳበት አንዳችም ነገር የለም:: ሰው ቅዱሳት መጻሕፍትን ተምሮ ከተጐዳ

ችግሩ ያለው ከራሱ ወይም ከመምህሩ እንጂ ከቅዱሳት መጻሕፍቱ ሊሆን አይችልም:: ችግር የሚፈጠረው በመንፈስ ቅዱስ አጋዥነት የተጻፈውን ቅዱስ መጽሐፍ በርኩስ መንፈስ አጋዥነትና በራስ ፈቃድ ተነሣሥቶ ለመተርጐም በሚሞከርበት ጊዜ ነው:: 2ጴጥ1፥20-21፣ የሐዋ8፥30-31 መንፈሳዊ ትምህርት ዓላማውን ሳይለቅ በሚገባ ቢማሩት ምንም ዓይነት ጉዳት የሌለው ፍጹም ጠቃሚ ትምህርት ነው::

ዓለማዊ (ሥጋዊ) ትምህርት ግን ፍጹምነት የለውም:: በየጊዜው በሚደረስባቸው አዳዲስ ግኝቶች የተነሣ በአቀራረጹ ብቻ ሳይሆን በመሠረታዊ ሐሳቡም ከጊዜ ወደ ጊዜ የመለዋወጥና እያደገ የመሄድ ባሕርይ አለው:: ይህ ሂደት ዘመናዊ ትምህርት ምንም እንኳን ጥልቅ ቢመስልም ገና ዕድገቱን ሙሉ በሙሉ ያልጨረሰ እንጭጭ እንደሆነና ፍጹምነት እንደሚጎድለው ያሳያል:: እስከ አሁንም ድረስ ወደ ሙሉ የዕውቀት ደረጃ ባለመድረሱ አዲስ ሐሳብ ሲገኝ ብቻ ጉዳታቸው የሚገለጥ ዛሬ ግን በጠቃሚነታቸው ብቻ ጉልተው የሚታወቁ ብዙ ስሕተቶችን አካቶ ይዟል::

የዘመናዊ ትምህርት ፅንሰ ሐሳቦች በሙሉ በቤተ ሙከራ ተፈትሸው የወጡ አይደሉም:: ሙከራ ሊደረግባቸው የማይችሉ ብዙ የዘመናዊ ትምህርት ክፍሎች አሉ:: እነዚህ በሙከራ ያልታዩ ይልቁንም በዕድል፣ በመላምትና በግምት የተገኙ ጭብጥ የሌላቸው ሐሳቦች (ሃይፖተቲካልስ) ጉድለታቸው እስኪታወቅ ድረስ የሰውን ልጅ በተሳሳተ አመለካከት ተቀርጾ እንዲያድግ በማድረግ፣ በማኅበራዊ ኑሮው፣ በጤናው፣ በምግባሩና በሃይማኖቱ ላይ ይህ ነው የማይባል አሉታዊ ተፅዕኖ ማሳደራቸው አይቀርም:: ይህም የዘመናዊ ትምህርት ዋነኛና ቀጥተኛ ጉዳት ተደርጐ ይጠቀሳል:: ሃይማኖት የሌላቸውና





ለመንፈሳዊ ነገር ግድ የሌላቸው ሰዎች ዘመናዊ ትምህርት ጥቅም ብቻ እንጂ ጉዳት ያለው አይመስላቸውም:: ነገር ግን ዘመናዊ ትምህርት በመንፈሳዊ ትምህርት ከተመዘነ በብዙ ጎዳና ሊጎዳ እንደሚችል መታዘብ ይቻላል::

## የትምህርት ተዛማጅ ጉዳቶች

1) ከላይ ከተጠቀሰው በተጨማሪ በዘመናዊ ትምህርት ምክንያት ሲከሠት የሚስተዋለው ጉዳት ሰዎች ለትምህርት ከሚሰጡት ጊዜ ጋር የተቆራኘ ነው:: ይኸውም አንዳንድ ሰዎች ትምህርት ለሰው ከሚያስፈልጉት ነገሮች እንደ አንዱ ብቻ በነጠላ ሊታይ የሚገባው ነገር መሆኑን ይዘነጉታል:: ለሚያስፈልጓቸው ሌሎች ተግባራት ማዋል ያለባቸውን ጊዜ በሙሉ ለትምህርት ብቻ በማዋል የኋላ ኋላ ሲጸጸቱ ይታያል:: ለምሳሌ:- አንዲት ልጃገረድ ትምህርቷን ባለመመጠንዋ ምክንያት የመውለጃ ዕድሜዋ ቢያልፍባት ተምራ ያገኘችው ማዕረግ የተሳናትን ልጅ መውለድ ሊመልስላት ወይም ኑሮዋን ደስተኛና የተሟላ ሊያደርገው አይችልም:: ስለዚህ ጊዜን አስፈላጊ ለሆኑ ነገሮች ማብቃቃት እንጂ መላ ዕድሜን ለትምህርት ብቻ መስጠት ብልህ አያሰኝም::

ትምህርት ሰው እራሱን ካልመጠነ በቀር ፍጻሜ የሌለው ነገር ነው:: አንድ ሰው በዓለም ላይ ያሉትን ነገሮች ጠቅሎ ሊያውቅ አይችልም:: በአንድ ርእስ ጉዳይ ግን የተሻለና ጠለቅ ያለ ዕውቀት ሊኖረው ይችላል:: ሐዋርያው «ከዕውቀት ከፍለን እናውቃለን» በማለት የተናገረው አንድ ሰው የሚያውቀው ጥቂት ነገርን ያውም በከፊል መሆኑን ለማስረዳት ነው::1ቆሮ13፥9

ጠቃሚ ነገር በልክ ተምሮ መሥራት ነው:: ብዙ ተምረው ምንም ሳይሠሩ ሕይወታቸው የሚያልፍ ሰዎች ቁጥር ጥቂት

አይደለም። ስለዚህ ትምህርትን መመጠን ነገር ግን ሥራን ማብዛት ይገባል። ጠቢቡ ሰሎሞን «ብዙ መጻሕፍትን ማድረግ ፍጻሜ የለውም፥ እጅግም ምርምር ሰውነትን ያደክማል።» በማለት የተናገረው ሰው የሚጠቀመው ብዙ በመማሩ ሳይሆን በልክ ተምሮ ብዙ ሲሠራ መሆኑን ለመጠቆም ብሎ ነው። መክ12፥12 በተጨማሪም ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ በልክ ስለመኖር የሰጠው ምክር በልክ ስለ መማርም ሊጠቀስ ይችላል። 2ጢሞ4፥5

መንፈሳዊያን ሰዎች መንፈሳዊ ትምህርት ቤትን እንደ መካነ ገድል (ገድል መፈጸሚያ ቦታ) በመቁጠር መላ ዘመናቸውን በትምህርት ቤት ለማሳለፍ ይወስናሉ። ይህ ድርጊት የዓለምን ጥቀርሻ ሳይቀቡና ከዓለም ምንም ሳይፈልጉ ለመኖር የሚወሰን የምናኔ ኑሮ በመሆኑ ጊዜን እንደ ማባከን አይቆጠርም። ታውቆ የተወሰነ ውሳኔ በመሆኑም ምንም ዓይነት ጸጸት አያስከትልም።

ሆኖም እንዲህ ያለ የምናኔ ሐሳብ የሌላቸው ሰዎች በመንፈሳዊ ትምህርትም ላይ ቢሆን ያለ አግባብ ጊዜ ማጥፋት የለባቸውም። ብዙ ተምሮ ምንም ሳያገለግሉ፣ የሚሹትንም ሳያገኙ እየተቆጩ ኖረው ከመሞት በመጠኑ ተምሮ የተማሩትንም በአግባቡ ተጠቅመውበት ማለፍ ይመረጣል። ቤተ ክርስቲያን ሕይወት የሚገኝበትን ጥልቅ መንፈሳዊ ትምህርቷን ለሰው ሁሉ እንዲዳረስ የበለጠ ጥረት ማድረግ አለባት።

እግረ መንገዴንም ሳልጠቁም የማላልፈው ነገር ቢኖር የሚመለከታቸው አካላት በሙሉ ቢያስቡበት ሰፋ ያለ ጊዜ የሚጠይቁት የንባብ፣ የቅዳሴ፣ የዜማ፣ የአቋቋም፣ የቅኔና የመጻሕፍት ትርጓሜ ትምህርቶቿ አሁን ከሚወስዱት እጅግ በጣም ባነሰ ጊዜ ውስጥ መጠቃለል የሚችሉ መሆናቸውን ነው። ይህ





እስከሚሆን ድረስ ደግሞ የመንፈሳዊ ትምህርት ጥማት ያለባቸው ምእመናን ሁኔታዎች እስከ ፈቀዱላቸው ድረስ በግላቸውም ቢሆን እንኳን ትምህርተ ቤተ ክርስቲያንን ከማጥናት መቦዘን የለባቸውም።

2) ሰው ምንም ቢማር ራሱን እንደ አዋቂ መቁጠር አይገባውም። አዋቂ እንደ ሆነ የሚሰማው ሰው በትዕቢት ይይዛል። «ማንም አንዳች ያወቀ ቢመስለው ሊያውቅ እንደሚገባው ገና አላወቀም።» 1ቆሮ8፥2 በማለት ቅዱስ ጳውሎስ ተናግሯል። መታወቅ ያለበትን ትህትናን ሳያውቃት ሰው አዋቂ ሊባል አይችልም። ትሕትና ደግሞ አዋቂ ነኝ አታሰኝም። በዚህ ዓለም ካሉት ነገሮች ከቁጥር የማይገባን ጥቂት ነገር አውቆ አዋቂ ነኝ ማለት እጅግ የሚያሳፍር ነው።

ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ «ዕውቀት ያስታብያል» 1ቆሮ8፥2 በማለት እንደተናገረው ዕውቀት ሲያስታብይ ፍቅር ግን ያንጻል። ከዕውቀት ፍቅር በብዙ ይበልጣል። ስለዚህ አንተ ብዙ ዕውቀት ቢኖርህ ትንሽ ፍቅር ያለው ሰው ይበልጥሃልና መታበይ አይገባህም።

ሰው ሁሉ ከትዕቢት ለመዳን ያወቀውን ዕውቀት ከሌሎች ሰዎች እንዳገኘውና በዕውቀት ከርሱ የተሻሉ በርካታ ሰዎች እንዳሉ ቢያስብ በጣም ይጠቀማል፡ ከዚህም በላይ ዕውቀትን እንደ ገበቴ ውኃ ማፍሰስ (ማጥፋት) የሚቻለው ፈጣሪም እንዳለ ባይዘነጋ ጥሩ ነው። ከአንተ አስቀድሞ የነበሩ ብዙ አዋቂዎች እንደ ቀለም ቀንድ ተሰብረው ተቀብረዋል። ሌሎችም የትምህርት ማስረጃቸውን እያሳዩ የሚለምኑ ሆነዋል። ከፊሎቹ ደግሞ አብደውና አእምሮአቸውን አጥተው የሚናገሩትን እንኳን አያውቁትም። ታዲያ አንተ ከእነዚህ እንደ አንዱ ባለመሆንህ ማመስገን ሲገባህ የምትኩራራው ከእግዚአብሔር እጅ የምታመልጥ ይመስልሃልን? ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ «ዕውቀትም

ቢሆን ይሻራል» በማለት የተናገረውን ቃል አስበህ ዕውቀትን የሚሰጥና የሚነሣ የሰማይን አምላክ አመስግን እንጂ አትታበይ:: 1ቆሮ13÷9

ትዕቢት በእጅጉ ይጎዳል:: አንተ በዕውቀትህ የምትታበይ ሰው ትዕቢት መጉዳቷን እንኳን ሳታውቅ አዋቂ ነኝ እንዴት ትላለህ? በማወቅህ ምክንያት ሊፈጠሩ የሚችሉ ትዕቢትና ትምክህት የሚያመጡብህ ጉዳት ትምህርት ከሚሰጥህ ጥቅም በእጅጉ ይከፋል:: ታዲያ ተምሮ ትዕቢተኛ ከመሆን ደንቆሮ ትሑት መሆን አይሻልም ትላለህን?

የአንድ የፈጠራ ሙያ ባለቤት ብትሆን እንኳን ልትመካ አትችልም:: ምክንያቱም እርሱም ቢሆን መሠረቱን ማየት ከቻልክ የሌሎች መሆኑን ትገነዘባለህ:: በዙሪያ የምታያቸው ነገሮች በአብዛኞቹ የአንድ ሰው የፈጠራ ውጤት ሳይሆኑ የብዙ ሰዎች የሐሳብ ጥርቅም ውጤቶች ናቸው:: ወይም በአንድ ሰው ከተጀመሩ በኋላ በሌሎች ሰዎች እየዳበሩ አሁን የምታያቸውን አኽለዋል:: ለምሳሌ:- መቀመሪያ (ኮምፒውተር)፣ ሰዓት፣ ስልክ፣ ነፋሰ ድምፅ (ሬዲዮ)፣ ነፋሰ ሥዕል (ቴሌቪዥን)፣ መብራትንና ሌሎችንም ነገሮች ብትመለከት ስለግኝታቸው አንድ መሠረት የጣለ ሰው ቢጠቀስላቸውም አሁን ላሉበት ደረጃ የበቁት ግን የብዙ ሰዎች ሐሳብ ተጨምሮባቸው ነው:: መሠረት ጣለ የተባለውም ሰው ከእርሱ በፊት የነበሩ ሰዎች ለግኝቱ መሠረት የሆነ ሐሳብ በሆነ መንገድ ባይለግሱት ኖሮ መሠረት የተባለውን ሐሳብ እንኳን ለማግኘት አይበቃም ነበር:: ከዚህ ሁሉ በላይ ዕውቀት የባሕርይው የሆነ የዕውቀት ባለቤት አእምሮውንና የተገለገለባቸውን ቁሳቁሶች ባይፈጥርለት ኖሮ ማንም ሰው የፈጠራ ሙያ ባለቤት ባልሆነም ነበር:: ታዲያ ይህን ሁሉ ያስተዋለ በፈጠራ ሙያው ፈጣሪን ማመስገን እንጂ መመካት አይገባውም::





የሚመካውን ግን ሐዋርያው እንዲህ ሲል ይገሥጻል:- «አንተ እንድትበልጥ ማን አድርጐሃል? ያልተቀበልከውስ ምን አለህ? የተቀበልህ ከሆንህ ግን እንዳልተቀበልህ የምትመካ ስለ ምንድር ነው?» 1ቆሮ4÷7

3) መንፈሳዊ ትምህርት መንፈሳዊ ዓላማ ሲኖረው ሥጋዊ ትምህርት ደግሞ በአመዛኙ ሥጋዊ ዓላማ አለው:: መንፈሳዊ ትምህርትን ከዓላማው ወጥቶ መብያና መጠጫ ቢያደርጉት ፈጣሪን ማስደሰት አይችልም:: አልፎ ተርፎም እንደ ቅኔ ባሉ መንፈሳዊ ትምህርት ፈጣሪን ለማመስገን መራቀቅ ሲገባ ፍጡርን ሲሹ እንደፈጣሪ ለማወደስ አልያም ደግሞ እንደ ዲያብሎስ ለመደምሰስ ቢጠቀሙበት ያለ ዓላማው ነውና ማስጠየቁ አይቀርም:: ስለዚህ በተማሩት ትምህርት ከመጠየቅና ከመጐዳት በአግባቡ በሥራ ላይ በማዋል መጠቀም ያሻል:: መኮትኮቻን መፍለጫ፣ መፍለጫን ደግሞ መኮትኮቻ ማድረግ ያለፋል እንጂ ምንም አይጠቅምም:: እንደዚሁም ሁሉ መንፈሳዊ ትምህርትን ያለ ዓላማው ቢያውሉት ያስጐዳል እንጂ አይጠቅምም::

4) ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ «የሰው ሕይወት በገንዘቡ ብዛት አይደለምና ተጠንቀቁ::» ሉቃ12÷15 በማለት አስተምሮአል:: የሰው ሕይወት በገንዘቡ ብዛት አይደለም ማለት ባለው ነገር መጠን አይደለም ማለት ነው:: ስለዚህ የሰው ሕይወት በጉልበቱ፣ በመልኩ፣ በወገኑ፣ በዕውቀቱ ልክ አይደለም:: አንዳንድ ሰዎች ግን ዛሬ ዛሬ ሕይወት በትምህርት ልክ መስሏቸዋል:: በዚህ ምክንያት በትምህርታቸው ማነስ ተስፋ በመቁረጥ በእጅጉ ያዝናሉ:: በዚህ ጉዳይ ብዙ ከማዘን መማር የሚችሉበት መንገድ ካለ መማር የሌለ ከመሰላቸውም ምንም ሳይማሩ የተሻለ ኑሮ የሚኖሩትን ሰዎች

በመመልከት እንርሱም እንደዚያ ከመኖር የሚያግዳቸው ነገር እንደሌለ በማመን ጠንክሮ መሥራት ይኖርባቸዋል:: ስለ ትምህርት ባለን የተዛባ አመለካከት የምንጐዳው እኛው ራሳችን ነን:: «ያልተማረ ይታሰር ወይም ይገደል!» ተብሎ እስካልታወጀ ድረስ ጥሩ አስተሳሰብና ስብእና ካለህ የምትሠማራበት የሥራ መስክ ይለይ ይሆናል እንጂ ከተማረ ሰውም በተሻለ መልኩ ለመኖር ትችላለህ:: ይህን መቀበል ካቃተህ ግን ትምህርት አምላኪ ከመሆንም ባሻገር ብትማርም እንኳን የትግል መንፈስ የለህምና ስኬታማ አትሆንም:: ስለዚህ ያልተማረ ብትሆንም ሙሉ ሰውነት ይሰማህ እንጂ አትሽማቀቅ:: አልተማርኩም ብሎ ተስፋ መቁረጥ ባልተማሩ ሰዎች ዘንድ አልፎ አልፎ የሚታይ የትምህርት አንጻራዊ ጉዳት ነው::

5) ለማወቅ ብትጓጓና ጎበዝ ተማሪ ለመሆን ብትመኝ መልካም ነው:: ምኞትህም ከግብ እስኪደርስ ጠንክረህ ተማር:: ሕይወትን መና በሚያስቀሩ ልዩ ልዩ ዕፀዋቶች ታግዘህ ለመማር አትሞክር:: አንዳንዶች ለጥናት ይረዳል በማለት ጫት ከመቃም አንሥቶ ዕውቀት ይገልጻሉ የተባሉትን ልዩ ልዩ ዕፀዋት በመጠቀም በጤናቸው፣ በጠባያቸውና በመሳሰሉት ማንነታቸው ላይ የማይሽር ጠባሳ አስቀምጠዋል:: ለመማር አገዙኝ የምትላቸው እነዚህ ዕፀዋት ሱስ ወደ መሆን ይለወጡና የሠራህበትን ገንዘብ በሙሉ «ያስተማርነበት ነው!» በማለት እንደሚያስገብሩህ መዘንጋት የለብህም::

6) ከተማርህ በኋላ በተማርከው የትምህርት ዘርፍ ተያያዥ የሆነ ሥራ ብታገኝ መልካም ነው:: ይህ ግን ሊሳካም ላይሳካም የሚችል ነገር በመሆኑ በመስክህ ሥራ አላገኘሁም ማለት ሥራ ፈጽሞ የለም ማለት አይደለም:: ማንኛውምን ሥራ ለመሥራት የተነሣሣ ልቡና ይኑርህ:: ገቢ ባይኖረውም እንኳን የሥራ ልምድ የሚሆንህን መንገድና ዕድል ተጠቀምበት እንጂ አትናቀው::





መሥራትም ትምህርት ነውና ገቢ ባይኖረውም ከመቦዘን መሥራት በጣም ጠቃሚ ነው:: ሥራ ስታጣ አስብና ፈጥረህ ሥራ እንጂ ሥራን ከመንግሥት ብቻ አትጠብቅ:: እንዲህ ማድረግ ተስፋ ከመቁረጥ ያድንሃል:: ተምረህ ሥራ ማጣትህ ካልተማረ ይልቅ ተስፋ ካስቆረጠህ መማርህም ያጠራጥራል:: ምክንያቱም መማር ማለት በተሻለ መልኩ ማሰብ ማለት ነዋ!

# ምዕራፍ ዐሥራ አንድ

## «መልካም ስም»

ጠቢቡ ሰሎሞን ስለ ስም ሲናገር «ከመልካም ሽቶ መልካም ስም ይሻላል» ብሏል:: መክ 7፥1 እግዚአብሔር ስምን የብዙ ነገሮች ምልክት አድርጎታል:: ስም መብት፣ ክብር፣ ገንዘብ፣ መርዳት፣ ችግር፣ ውድቀት፣ ሲሆን ለማየት በዙሪያህ ያሉትን ነገሮች መመርመር ብቻ በቂ ነው:: ምንም የሚያስከብር ነገር ሳይኖራቸው በቀደመ ማንነታቸው ብቻ ሰዎች ሲከበሩ አይተህ አታውቅም? በስም ብቻ ገንዘብ የሚገኝበት ሁኔታስ ገጥሞህ አያውቅም?

ነገር ግን ብዙ ወጣቶች «መልካም ስም» ያለውን ከፍተኛ ዋጋ አያውቁም:: እንዲህ የሚያስብለው ስማቸውን በክፉ የሚያጠፋ ርካሽ ተግባር ዘወትር ሲፈጽሙ መገኘታቸው ነው:: መጥፎ ነገሮች ምን ጊዜም ክፉ ስም ያስገኛሉ :: በሥውርና በድብቅ ቢፈጸሙ እንኳን ከጥቂት ቆይታ በኋላ በአደባባይ መውጣታቸው የማይቀር ነው:: «ድብቁን የምትገልጽ የውስጡን ወደ ውጭ የምታወጣው ሆይ» የሚባል እግዚአብሔር ሥራውን አይዘነጋምና::

መልካም ስም ከመልካም ሽቶ ጋር የተነጻጸረው ያለ ምክንያት አይደለም:: መልካም ሽቶ ርቆ ሄዶ ከመሽተቱም በላይ ስሜትን ይማርካል፤ ይስባል:: መልካም ስምም አንተ ካላሰብከው ቦታ ደርሶ ያሳውቅሃል፣ ያስወድድሃል:: ክፉ ስም ደግሞ እንደ ክፉ ሽታ ነው:: ያ ከሩቅ መጥቶ እንደሚበክል ተደብቆ የተሠራም ክፉ ሥራ ርቆ





ሄዶ ስምን ይበክላል:: ስለዚህ በዘመንህ ሁሉ ከቁሳዊና ከብልጭልጭ ነገሮች ይልቅ ጥሩ ስም እንዲኖርህ ተጣጣር። መልካም ስም ካለህ የተመኘኸውን ሁሉ ሳታገኝ አትቀርምና:: መልካም ስም የመልካም ሥራ ነው እንጂ የፈጠራና የማስመሰል ውጤት አይደለም::

መልካም ስም ያለውን ጠቀሜታ ለመረዳት ቀላል ነው:: እንኳን በብዙ አቅጣጫ ብዙ መልካም ስም ኖሮህ ይቅርና «እገሌ ታማኝና እውነተኛ ነው» በሚል ስም ብቻ ብትታወቅ ብዙ ጥቅሞች ይከቡሃል:: ለምሳሌ፡- እውነተኛ ሰው በብዙዎች ዘንድ ታማኝነትና አክብሮትን ያተርፋል:: የሚያገኙቸው ወዳጆቹ እውነተኝነቱን አድንቀውና ወደው የሚቀርቡ በመሆናቸው አብዛኞቹ ራሳቸው እውነተኞች መሆናቸው የማይቀር ነውና፤ እውነተኛ በመሆንህ እውነተኞች ጓደኞችን እንድታገኝ ረዳህ ማለት ነው:: ይህ ደግሞ ታላቅ ትርፍ ነው:: የሰው ሁሉ ችግር ታማኝ ባልንጀራ ማፍራት አለመቻል ነውና::

ከዚህም ሌላ በመልካም ስም መታወቅ ሌላም የሚያስገኘው ጥቅም አለ:: የንግዱ ዓለም ብዙ ማጭበርበር ያለበት መሆኑ ይታወቃል:: ሆኖም አሠሪዎችና ሠራተኛ ቀጣሪዎች ለታማኝነት ከፍ ያለ ዋጋ ሰጥተው እውነ ኞችንና ታማኞችን መቅጠር ይፈልጋሉ:: ስለዚህ አንተ በታማኝነት መታወቅህ ብቻ በሥራ ችሎታ ብዙ የሚበልጡህ ሰዎች ቢኖሩም እንኳን ሥራ የማግኘትና ሌሎች ከሥራ በሚባረሩበትም አጋጣሚ በሥራህ የመቆየት ዕድል ይገጥምሃል:: ይህም «ታማኝ» የሚል መልካም ስም ማትረፍ ብቻ ምን ያህል እንደሚጠቅም ያስረዳል::

ባልና ሚስት በታማኝነት የሚተዋወቁ ከሆነ ጥርጣሬንና አለመተማመንን አስወግደው በፍቅር ለመኖር ይረዳቸዋል። ታማኝ ልጆችም በወላጆቻቸው ዘንድ ሙሉ አመኔታን ያተርፋሉ። ልጆች በወላጆች ዘንድ «ታማኝ» በሚል መልካም ስም ከታወቁ ቀስ በቀስ ሰፊ ነፃነት እያገኙ ይመጣሉ። እውነቱን መናገር ተግሣጽን እንኳን ቀላል የሚያደርግበት ሁኔታ አለ። አንድ ታዳጊ አጥፍቶ በሚቀጣበት ጊዜ ቢክድ የቅጣቱ መጠን ሊጨምር ይችላል። ቢያምንና ይቅርታ ቢጠይቅ ግን ቅጣቱ ይቀልለታል። በወኅኒ ቤትም ሆነ በእግዚአብሔር ዘንድ ቢሆን ሐቁ ይህ ነው።

ሰው ሁሉ በሕይወት ዘመኑ ሌሎች እንዲያምኑትና ቃሉን እንዲቀበሉት በብርቱ የሚፈልግበት አንድ አጋጣሚ ሳይመጣበት አይቀርም። ታማኝ የሚል ስም ያለው ሰው በዚህ ሁሉ ሳይቸገር ነገሩን ሌሎች በቀላሉ ሊያምኑለት ይችላሉ። በአጠቃላይ «ታማኝ» የሚል መልካም ስም ያተረፈ አንድ ሰው ተዘርዝረው የማያልቁ ብዙ ጥቅሞችን ያገኛል።

ከላይ የተጠቀሰው ስለ «ታማኝነት» ብቻ ነው። ከዚህ በተጨማሪ ሐቀኛ፣ የተከበረ፣ ጨዋ፣ ሰው አክባሪ፣ ቁጥብ፣ ቁም ነገረኛ፣ ዐዋቂ፣ ትሑት፣ የሚሉ ሌሎች መልካም ስሞችን ብታተርፍ ምን ያህል በነፍስና በሥጋ እንደምትጠቀም ገምት። እነዚህ ነገሮች ያሉት ለሥራ፣ ለጓደኝነት፣ ለትዳር በአጠቃላይ ለሁሉም ጉዳይ በመብራት እንደሚፈለግ ጥርጥር አይኑርህ።

መልካም ስም እንዲሁ በቀላሉ አይገነባም። ብዙ ድካምና ጥረት ከመጠየቁም ሌላ ብዙ ጊዜ ይወስዳል። የሚያስደንቀው ግን ጥሩ ስም ሲበላሽ ምንም ጊዜ አለመፈለጉ ነው። ስለዚህ መልካም





ስምን እንደ ዓይን ብሌን ሊጠነቀቁለት ይገባል። መልካም ስም ገንዘብ፣ የትምህረት ደረጃ ወይም ሌላ መስፈርት አይጠይቅም። ፈቃደኛ ከሆንክ የነፍስህ ዕውቀት ብቻ መልካም ስም እንዲኖርህ ለምትሠራው ሥራ ሁሉ በቂ ናት።

የመልካም ስምን ጠቀሜታ መዘርዘር በአንፃሩ የመጥፎ ስምን ጉዳት መዘርዘር ነው። በመጥፎ ስም ከታወቅህ የእናትህ ልጅ እንኳን አያቀርብህም። ስለዚህ በሰካራምነት፣ በቅብጠት፣ በአባካኝነት፣ በውሸት፣ በቀልድና በመዘበት፣ በመልከስከስ፣ በገንዘብ ወዳድነት፣ በትዕቢት፣ በክህደት፣ በስሜታዊነት፣ በተናጋሪነትና በመሳሰሉት መጥፎ ስሞች እንዳትታወቅ ተጠንቀቅ። በገዛ እጅህ ሁሉ ነገር ርቆብህ ቁጭ ብለህ የምታለቅስበትን የኀዘን ገመድ ለምን ትጎትታለህ?

ወጣት ከሆንክ መጥፎ የተባሉትን ነገሮች ለመላቀቅ አልቻልኩም አትበል። አስቀድሞ እንደተገለጠው መጥፎና ጥሩ ነገር የሚወስዱት ጊዜ የተለያየ ነው። ከክፉ ጠባዬ ብታረምም ተቀባይነት ግን አላገኘሁም በማለት ተስፋ መቁረጥ አይገባም። ይህ ሁሉ የመጀመሪያ ክፉ ሥራህ ደሞዝ እንደሆነ አምነህ ራስህን እየወቀስህ ከትላንቱ ይልቅ ዛሬ ተቀባይነት ለማምጣት ተጣጣር እንጂ ወደ ኋላህ አትመለስ። መቼም ቢሆን «ከመልካም ሽቶ መልካም ስም» ይሻላልና። መክ7፥1

አንተ ጥሩ የትምህርት ደረጃና ሙያ ይዘህ ሥራ አጥተህ ስትቀመጥ መልካም ስም የያዙ ሌሎች ያለምንም ማስረጃና የሥራ ልምድ የምትቀናበትን ሥራ ሲሠሩ አይተህ አታውቅምን? ይህ አገላለጽ ትምህርትና ዕውቀትን ለማቃለል ሳይሆን የመልካም ስምን

ታላቅነት ለማጉላት ነው። በትምህርትና በሥራ ልምድህ ላይ የመልካም ሥነ ምግባር ባለቤት መሆንህ ከተነገረ ውጤቱ ምን ሊሆን እንደሚችል መገመትም አያስቸግርም።

የመልካም ስም ቁልፉ መንፈሳዊነት ነው። ትምህርተ ሃይማኖትና ፈሪሃ እግዚአብሔር ያለው ሰው በሥነ ምግባር መታነፁና የመልካም ስም ባለቤት መሆኑ አያጠራጥርም። የዚህ ዓለም ምስኪን ማለት መንፈሳዊ ተብሎ መልካም ስም የሌለው ነው። መልካም ስም እንዲኖርህ ትፈልጋለህ? ታዲያ ገጸ ልቡናህን ወደ ፈጣሪህ ለምን አትመልስም?

## «ኀፊረ ገጽ»

እግዚአብሔር በሰው ልጆች መካከል መተፋፈር እንዲኖር አድርጓል። ይልቁኑም «ወከደና በኀፍረት» እንደ ተባለው ሴቶች በማፈር እንዲያሸበርቁ ልዩ መጐናጸፊያ ሰጥቷቸዋል።

«ኀፊረ ገጽ» ማለት የሌላውን ሰው ገጽ አይቶ መፍራትና ማፈር ማለት ነው። ይህ እጅግ ውድ ስጦታ ነው። በመፍራት ውስጥ ማክበር በማክበር ውስጥ ደግሞ መፍራት እንዳለ ሁሉ በማፈርም ውስጥ ማክበርና መፍራት አለ። ሰውን የማይፈራ እግዚአብሔርንም አይፈራም ለማለት ያስደፍራል። ምክንያቱም ሰውን መፍራት እግዚአብሔርን የመፍራት መገለጫ ነውና። 1የሐ3÷17

ቅዱሳት መጻሕፍት መፍራትና ማፈር የማያውቅ ደረቅ ሰውን ያወግዛሉ። ማር ይስሐቅ ከሌላ መጽሐፍ ያገኘውን «ዘኢየኃፍር ገጸ ከይሲ ውእቱ ዘይሲሰይ መሬተ» ፤ «የሰውን ገጽ አይቶ የማያፍር አፈርን እንደሚበላ እባብ ነው» ማለት ነው።





ቅዱሳን አበው የሃይማኖት ዓይን ስላላቸው እንኳን በአካል ገዝፎ በአጠገባቸው የሚገኝ ሰውን ይቅርና የሚጠብቃቸውን መልአክ በማፈር ከማያስፈልጉ ነገሮች ሁሉ ተጠንቅቀው ይኖሩ ነበር። ሊላው ቀርቶ ጠባቂ መልአካቸውን በማፈር ለብቻቸው ሳሉ እንኳን ከልብስ ተራቁቶና ተገላልጦ ዘና ማለት የማይሆንላቸው እንደ ነበሩ ዜና ሕይወታቸው ይናገራል።

በእርግጥ የማያሳፍርና የሚያሳፍር ነገርን ለይቶ ማወቅ ለሰው ሁሉ የሚገባ ነገር ነው። ምክንያቱም ከመለመዱ የተነሣ የማያሳፍረው ሲያሳፍር፤ የሚያሳፍረው ደግሞ ሲያስመካ ማየት የዘወትር ክሥተት እየሆነ መጥቷልና።

በዚህ ዘመን ውሸት በሚናገሩበትና በሚያታልሉበት ጊዜ ፊትን ሳያጥፉ ድርቅ ብሎ መፋጠጥ እንደ ጉብዝና ተቆጥሯል። ይህን የሚያደንቁና ሲዋሹ የሌላውን ፊት ትኩር ብሎ ለማየት ራሳቸውን የሚያለማምዱ በርካታ ሰዎች በዙሪያችን ይገኛሉ። ለጊዜው ይህ ጉብዝና ሊመስል ይችል ይሆናል ውሎ አድሮ ግን ከፍተኛ ጸጸት ማስከተሉ አይቀርም።

አፋራምነት የመልካም ሥነ ምግባር መገለጫ ነው። ሆኖም ብዙዎች እንደ ጭቆናና ብዝበዛ መሣሪያ አድርገው ስለሚቆጥሩት በምንም አጋጣሚ ማፈር አይፈልጉም። እንዲያውም አንዳንድ ደፋር ነን ባዮች ዓይናፋርነትህን አውቀው በአንድ ወቅት ሳያሸሯብህና ሳያስጨንቁህ አይቀሩም። ይህ አጋጣሚ ራስህን በጣም እንደ ተጠቃ ሰው ቆጥረህ እንደ እነርሱ «ደረቅነትን» ለመለማመድ በቁጣ እንድትነሣሣ ለማድረግ ለሰይጣን በር ይከፍትለታል። ስለዚህ ይህንና ይህን የመሳሰሉ ገጠመኞች ዓይናፋርነትህ ብዙ እንዳጐደለብህ እንዲሰማህ በማድረግ እንድታማርረው ወይም ደግሞ እሽቀንጥረህ

እንድትጥለው ያደርጉሃል:: ነገር ግን ይህን ካደረግህ በዚህ ዓለም ስትኖር በባሕር ላይ ሆነህ መልሕቅህን እንደ ጣልከው ቁጠር::

ኀፊረ ገጽ ብተለይ በወጣትነት መንፈሳዊ ሕይወትን ለመምራት በእጅጉ ይጠቅማል:: ተገቢ ባልሆነ ተግባርህ ብቻህን ስትሆን ሕሊናህን፣ በቤት ውስጥ ወላጆችህን፣ በሌላ ስፍራ ደግሞ አለቆችህን፣ መምህራንንና ሌሎች ታላላቅ ሰዎችን ማፈርና ማክበር ይኖርብሃል:: ሰው እኮ የሚመከረው ሕሊና ሲኖረው ወይም የሚፈራውና የሚያከብረው ሰው ሲኖረው ነው:: እነዚህ የሌሉት በማን ይመከራል?

ማፈርና መፍራት ከሰዎች እየራቁ በመሄዳቸው በሀገራችን ብዙ ችግሮች ተበራክተዋል:: ሽማግሌን አፍሮ መታረቅ እንኳን እንደ ከዚህ ቀደሙ ቀላል ነገር አልሆነም:: ብዙ ሴቶች እኅቶቻችን ለሻካራ ንግግርና «ደረቅ» ለሚያሰኛቸው አለባበስ ተጋልጠዋል:: በየፌርማታው፣ በየመጓጓዣ መኪና፣ በየመንገዱና በየፈፋው መሳሳምና መዳራት አበጀህ እንደሚያሰኙ ተግባራት ተደርገው ተወስደዋል:: በሀገራችን በኢትዮጵያ ከጥቂት ዓመታት ወዲህ ደግሞ መደባበቁና ጨለማን ተገን ማድረጉ ቀርቶ በሕዝብ መድረኮችና በአደባባይ ላይ በዝሙት መንፈስ መዳራትና መሳሳም የጥበብ መገለጫ ሆነው በየፊልሙና በየድራማው መሃል እንደ ሳጋ ተሰግስገው ይታያሉ:: በዚህ ፍጥትነታችን ከቀጠልን ዝሙትን እንደ ባህል እንደሚቆጥሩ ሀገሮች ግብረ ዝሙትን በገሃድ በፊልምና በቴአትር ቤቶች መድረክ የምናይበት ጊዜ ሩቅ አይሆንም::

የዚህ ሁሉ ምንጩ ኀፊረ ገጽ ከኢትዮጵያውያን ልቡና ተገፍቶ እንዲወጣ ስለተደረገ ነው:: ይህም ሁሉ ሆኖ ወጣቶች ገና ባለመንቃታቸው ዓለም ዓይናቸውን በጨው ላጠቡ ሰዎች





እንደምትመች አድርገው በመቁጠር ራሳቸውን «ደረቅ» ለማድረግ ይጥራሉ::

ለበጎና ለሚገባ ነገር ደፍሮ መሰለፍ ስማዕትነት ነው:: ነገር ግን ለሰይጣን ፈቃድ ደፍሮ መሰለፍ ምን ይባላል? ክርስቲያን አፋራም ነው ማለት ለመብቱ አይከራከርም፣ ዝም ብሎ ይጨቆናል፣ ይረገጣል ማለት አይደለም:: ማፈር የማይፈልግ ሰው ከሚያሳፍሩ ነገሮች መለየት ይገባዋል እንጂ ደፋርነትን መለማመድ መፍትሔ አይሆንም::

ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ የኤፌሶን ክርስቲያኖችን በመከረበት አንቀጽ «...የሚያሳፍር ነገርም፥የስንፍና ንግግርም ወይም ዋዛ የማይገቡ ናቸውና አይሁኑ::» በማለት ተናግሯል:: «የሚያሳፍር ነገርም» ሲል ሐሳብም፣ ንግግርም፣ ሥራም የሚያሳፍሩ ሊሆኑ እንደሚችሉ ይገልጻል:: እነዚህ ሦስቱም «ነገር» ይባላሉና:: ኤፌ5፥4

ከሥነ ተዋልዶ ጋር ግንኙነት ያላቸውን የሰውነት ክፍሎች፣ ፆታ ነክ ተግባራትን፣ ፆታ ነክ ውይይቶችን ማየት መስማት፣ ማውራትና ማከናወን በሕግ በሥርዓት፣ በልክና በፈሊጥ መሆን አለበት:: እነዚህ ነገሮች ከማፈር ጋር ቀጥተኛ የሆነ ግንኙነት አላቸው:: የእነዚህ ነገሮች በሙሉ ጌጣቸው ማፈር ነው:: ማፈር የሌለበት የሥነ ተዋልዶ አካል እንደ አሻንጉሊት አካል ነው:: ምነው? ቢባል ግብረ ነፍስ የለበትምና ስለዚህ ነው:: ማፈር ደግሞ የለባዊት ነፍስ ጠባይ እንጂ የሥጋ መታወቂያ አይደለምና::

ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ማፈር አለማፈርን በቀጥታ ከአለባበስ ጋር አያይዞ ገልጾታል:: «እንዲሁም ደግሞ ሴቶች በሚገባ ልብስ ከእፍረትና ራሳቸውን ከመግዛት ጋር ሰውነታቸውን ይሸልሙ::» 1ጢሞ2፥10 አንቺ ወጣት «በሚገባ ልብስ» በማለቱ የሚገባና የማይገባ ልብስ እንዳለ ሐዋርያው መናገሩን አስተዋልሽን?

ራስሽን መሸለም (ማስጌጥ) ከወደድሽም እንደ ሐዋርያው ምክር «ከእፍረት» ጋር አድርጊው ያለ እፍረት ብታጌጪ ጌጥሽ ጌጥ አይሆንም:: ታላቁ ጌጥ «ኀፈረ ገጽ» ነውና::

## ስኬታማነት

ወጣት ከሆንክ ቢያንስ አንድ ነገር እንዴት እንደሚሳካልህ ሳያስጨንቅህ አይቀርም:: የምታስበው ሁሉ እንዲፈጸምልህና ስኬታማ ሰው እንድትሆን ትፈልጋለህ? ከፈለግህ በመጀመሪያ በሕይወትህ መንፈሳዊ ሰው ሁን:: የስኬት መሠረት መንፈሳዊነት ነውና:: እንዲህ ሳትሆን ብዙ ነገር ቢሳካልህ እንኳን ተመልሶ እንዳልተወጠነ ሊሆን እንደሚችልና ውሸት እንደ ሆነ አስብ::

ማንም ሰው ደስተኛና ስኬታማ ሆኖ መኖር ይፈልጋል:: ወጣቶችም ይህን መፈለጋቸው መልካም ነገር ነው:: ስኬታማ ዕድሜን ያረዝማል፣ በተስፋ፣ በጥንካሬ ያቆያል:: መቸገር፣ ማጣትና ማዘን ግን ያለጊዜው ያስረጃል:: ደራሲው «እንበለ ጊዜ በላህ ኢይርሳዕ ወሬዛ» እንዳለ «ያለ ጊዜዬ በኀዘን ምክንያት እንዳላረጅ» ለማለት ነው:: (መልክዐ ሚካኤል) ሆኖም ግን ደስተኛና ስኬታማ ለመሆን መታወቅ ያለባቸው ብዙ ነገሮች አሉ::

ፍሬያማ ግብር (ስኬት) ማለት ሰው በሥጋዊ ሕይወቱ ተጨባጭ የሆኑ ነገሮችን ማግኘቱ ብቻ አይደለም:: የሰው መንፈስም (ነፍስም) የምትመኘው ብዙ ነገር አላት:: የነፍስ ምኞቶች በሙሉ እንደ እርስዋ ረቂቃን ናቸው:: የነፍስ ምኞቶች ሐዋርያው «የመንፈስ ፍሬዎች» በማለት የገለጣቸው ሲሆኑ እነርሱም:- ፍቅር፣ ደስታ፣ ሰላም፣ ትዕግሥት፣ ቸርነት፣ በጎነት፣ እምነት፣ የውሃትና ራስን መግዛት ናቸው:: ገላ5፥22 ሰው ስንል ነፍስም ሥጋም እንደመሆኑ መጠን በሥጋ የሚመኛቸው ግዙፋን ነገሮች ስለተሟሉለት ብቻ





ደስተኛና ስኬታማ ሊባል አይችልም:: ከላይ የተጠቀሱት «የመንፈስ ፍሬዎች» የሌሉት ሰው ስኬታማ አይደለም::

በብዙ ወጣቶች ዘንድ ያልተስተዋለ አንድ ነገር አለ:: ይኸውም ፍሬያማ ግብር (ስኬት) ማለት የተመኙትን ሁሉ ማግኘት ይመስላቸዋል:: ነገር ግን ከዚህ የሚበልጥ ስኬታማነት አለ:: እርሱም ራስን በመግዛት ምኞትን መመጠን ነው:: ምኞትን ከመመጠን ጋር ስናወዳድረው የተመኙትን ለማግኘት መልፋት በጣም ቀላል ነገር ነው:: ከባዱ ነገር አለመመኘት ወይም ምኞትን በልክ ለማድረግ መቻል ነው::

ታዋቂና ዝነኛ ሰው መሆን ብትፈልግ ብዙ ጥረትና ጊዜ ይፈጅብህ ይሆናል እንጂ ታገኘዋልህ:: ነገር ግን የተናቀ ሰው ለመሆን አስበህ ታውቃለህን? ብታስበውስ የሚቻል ይመስልሃልን? ትልቅ ሰው ከመሆን ትንሽ ሰው መሆን እጅግ ይከብዳል:: ታዲያ ችሎታ መባል ያለበት የቱ ነው? ትልቅ ሰው መሆን ባትችል እንኳን ጥረቱ ያም ባይሆን ፍላጎቱ ይኖርሃል:: ስለዚህ ትንሽ ነህ አትባልም:: ትንሽ ለመሆን ግን እንኳን መጣር ይቅርና ሐሳቡንም አምኖ ለመቀበል ይከብድሃል:: ለምን ይመስልሃል? ትንሽ ስለ ሆንክ ይመስልሃልን? አይደለም:: እንደዚህ ለማድረግ ችሎታ ስላሌለህ ነው::

በወጣትነት ዘመን ይህ የተሳካላቸው ያለ ምንም ጥርጥር ጻድቃንና ቅዱሳን ናቸው:: ለዚህ ማዕረግ የበቁት ብዙ ሀብት በማካበትና ብዙ በመማር ሳይሆን የኢየሱስ ክርስቶስን ፈለግ በመከተል ራሳቸውን ብዙ ስላዋረዱ ከዚህም ዓለም ምንም ስላልፈለጉ ነው::

ቅዱስ ዳዊት ያሰበውና የሚሠራው ሁሉ የሚከናወንለት ምስጉን ሰው ምን ዓይነት ሰው እንደ ሆነ ሲገልጽ እንዲህ ይላል:-

«ምስጉን ነው ፥ በክፉዎች ምክር ያልሄደ፥በዋዘኞችም ወንበር ያልተቀመጠ:: ነገር ግን በእግዚአብሔር ሕግ ደስ ይልዋል፥ሕጉንም በቀንና በሌሊት ያስባል:: እርሱም በውኃ ፈሳሾች ዳር እንደተተከለች፥ፍሬዋን በየጊዜዋ እንደምትሰጥ፥ ቅጠልዋም እንደማይረግፍ ዛፍ ይሆናል» ይልና በመጨረሻም «የሚሠራውም ሁሉ ይከናወንለታል» ይላል:: ከዚህ የበለጠ ስኬታማነት ሊኖር አይችልም:: ይህ የሚገኘው ደግሞ ከላይ የተገለጡትን መንፈሳዊ ጎዳናዎችን በመከተል ነው:: የስኬት መሠረት መንፈሳዊነት ነው የተባው ስለዚህ ነው::

ሰው ከእግዚአብሔር ርቆ ስኬታማ መሆን አይችልም:: የያዕቆብ ልጅ ዮሴፍ በሥጋም ሆነ በነፍስ ነገሮች ሁሉ የተሳኩለት ወጣት እንደ ነበር መጽሐፍ ቅዱስ ይመስክራል:: «እግዚአብሔርም ከዮሴፍ ጋር ነበረ፥ ሥራውም የተከናወነለት ሰው ሆነ፣ በግብፃዊው ጌታውም ቤት ነበር:: ጌታውም እግዚአብሔር ከእርሱ ጋር እንዳለ፣ እርሱ የሚሠራውም ሁሉ እግዚአብሔር በእጁ እንዲያከናውንለት አየ::»

ዛፍ ከግንዱ ተለይቶ ለማፍራት እንደማይችል እንዲሁ የሰው ልጅም ከፈጣሪው ተለይቶ ፍሬያማ መሆን አይችልም:: ሰው ሠራሽ አበባ መልኩ ይመር እንጂ ምንም ዓይነት መልካም መዓዛና ሕይወት እንደሌለው ሁሉ በችኮላና ከፈጣሪ ተለይተው ያፈሩት ነገር ሁሉ ውስጣዊ ደስታና ዘላቂነት የሌለው በመሆኑ መጨረሻው አሳዛኝ ነው:: ብዙ ነገር ኖሮህ በኃዘን ከመዋጥህ የተነሣ ምንም እንደሌለው ከምትሆን ትንሽ ነገር ኖሮህ በደስታ ብትኖር አይሻልህምን? ስለዚህ «የሰው ሕይወቱ በገንዘቡ መጠን አይደለምና» ነገሮችን መሻትህ ከፈጣሪህ እንዳይለይህ ተጠንቀቅ! ከመጎምጀትም ተጠበቅ! ሉቃ12÷15





ሰው ሁሉ ከእግዚአብሔር ጋር ቢሆን ነገሮች ሁሉ ይሳካሉ፣ ይከናወኑማል:: ራሱ ፈጣሪ «ያለ እኔ ምንም ልታደርጉ አትችሉም» ብሏልና:: ዮሐ15÷4-7 ያለ ረድኤተ እግዚአብሔር መማር ማስተማር መጻፍ መደጎስ በአጠቃላይ ማንኛውም ሥራ ከፍጻሜው ሊደርስ አይችልም:: ነቢዩ ነህምያም «እኛ ባሮቹ ተነሥተን እንሠራለን የሰማይ አምላክም ያከናውንልናል» ያለው «ማከናወን» የፈጣሪ ድርሻ ስለሆነ ነው:: ቅዱስ ዮሐንስ «ወጢንሰ እምኀበ ሰብእ» በማለት እንደተናገረው «መጀመር» የሰው ድርሻ ሲሆን መፈጸም ግን የእግዚአብሔር ነው:: ነገሮች ከፊጻሜ ሳይደርሱ ደግሞ ስኬት የሚባል ነገር ሊኖር አይችልም:: ስለዚህ «መፈጸም» የፈጣሪ ከሆነ የሰው ስኬት የተያዘው በእግዚአብሔር እጅ ነው ማለት ነው::

መንገድ እንዲቃናልህ የምትሠራውምሁሉ እንዲከናወንልህ ትፈልጋለህ? እንግዲያውስ ከዚህ በታች የሰፈረውን የመጽሐፍ ቅዱስ ቃል በልብህ አኑረህ ተጠቀምበት:: ቃሉም እንዲህ ይላል:- «የዚህ ሕግ መጽሐፍ ከአፍህ አይለይ፣ ነገር ግን የተጻፈበትን ሁሉ ትጠብቅና ታደርግ ዘንድ በቀንም በሌሊትም አስበው፤ የዚያን ጊዜም መንገድህ ይቀናልሃል ይከናወንልሃልም::» ኢያ1÷8

## «በጉብዝናህ ወራት ፈጣሪህን አስብ»

ጠቢቡ ሰሎሞን ለወጣቶች በሙሉ ዘለዓለማዊ መመሪያ የሚሆን የሕይወት ቃል ተናግሯል:: ቃሉም «የጭንቀት ቀን ሳይመጣ በጉብዝናህ ወራት ፈጣሪህን አስብ» የሚል ነው:: መክ12÷1 «በጉብዝናህ ወራት» ያለው ወጣቶችን ለመጥቀስ ፈልጎ መሆኑ ግልጽ ነው:: ወጣቶች «ጎበዞች» ይባላሉና:: ቅዱስ ዮሐንስ ወንጌላዊ በመልእክቱ «ጎበዞች ሆይ ብርቱዎች ስለ ሆናችው የእግዚአብሔርም ቃል በእናንተ ስለሚኖር ክፉውንም ስለ አሸነፋችሁ እጽፍላችዋለሁ::»

ብሎ በጻፈ ጊዜም ወጣቶች «ጎበዞች» እንደሚባሉ ማጠናከሪያ ሰጥቷል:: 1ዮሐ3÷14

«ክፉውንም ስለ አሸነፋችሁ» ማለቱም «ክፉ» የሚባለውን የወጣትነት ምኞት ስለ አሸነፋችው ማለቱ ነው:: ቅዱስ ጳውሎስ «ከክፉ የጎልማስነት ምኞት ሽሽ» በማለት የክርስትና ልጁ ጢሞቴዎስን እንደመከረው የወጣትንት ምኞት «ክፉ» ይባላልና:: ወጣቶች ፈጣሪያቸውን ማሰብ እንደሚኖርባቸው ተለይተው የተጠቀሱት ለምንድር ነው? ፈጣሪን ማሰብ ማለትስ እንዴት ነው?

በመሠረቱ ፈጣሪን ማሰብ የሚኖርባቸው ወጣቶች ብቻ አይደሉም:: ልጆችም ሆኑ አረጋዊያን ፈጣሪን ማሰብ ይኖርባቸው:: ጠቢቡ ሰሎሞን ግን ወጣቶችን ለይቶ ፈጣሪን ማሰብ እንዳለባቸው የተናገረበት ምክንያት አለው:: ይኸውም ከልጆችና ከአረጋዊያን ይልቅ ወጣቶችን እግዚአብሔርን እንዲረሱ የሚገፋፋቸው ብዙ ነገር ስላለ ነው::

እግዚአብሔርን ማሰብ ማለት ሕጉንና ትእዛዙን በቤት ሲቀመጡ፣ በመንገድ ሲሄዱ፣ ሲተኙና ሲነሡም መጫወት ማለት ነው:: ዘዳ6÷4-9 በተጨማሪም ቃሉን በልቡና መያዝና በፍጹም ልብና በፍጹም ነፍስ እግዚአብሔርን መውደድ ማለት ነው:: በዚህ መልኩ ፈጣሪን ማሰብ ይገባል:: ለምን ቢባል? ነቢዩ ዳዊት «እግዚአብሔርን የሚረሱ ይጠፋሉ::» ብሏልና::

ፈጣሪን ማሰብ ማለት «ሕጉን በቀንና በሌሊት ያስባል» በማለት ቅዱስ ዳዊት እንደ ተናገረው የእግዚአብሔርን ሕግ በደስታ ማሰብ ማለት ነው:: መዝ1÷2 ተግባር የተለየው ማሰብ ብቻውን ምግባር የተለየው እምነት ሆነ ማለት ነው:: ምግባር የተለየው እምነት ደግሞ





ነፍስ እንደ ተለየው ሥጋ የሞተ መሆኑ በግልጽ ተነግሯል:: ያዕ1÷26

እግዚአብሔርን ማሰብ ማለት በሥራ በሚገለጥ ነገር እግዚአብሔርን ማክበር ማለት ነው እንጂ በቃልና በአንደበት ብቻ አይደለም:: እግዚአብሔርን አስበዋለው ማለት በሥራ ካልተገለጠ ምንም አይጠቅምም:: ሚስት ለባሏ «ሁል ጊዜ አስብሃለሁ እናፍቅሃለሁ ከራሴ አብልጬ እወድሃለሁ» ብትለው ነገር ግን ባሏ ከሚወደው ነገር አንዱንም ባትሠራ «እወድሃለሁ» ማለቷ ብቻ ባሏን ሊያስደስተው ይችላልን? ፈጣሪንም ብዙ ትእዛዛቱን ወደ ኋላ ጥሎ «አስብሃለሁ» ማለት ብቻ ምንም አያስደስተውም::

ሩቅ ሀገር ያለ ወዳጃችንን በደስታው ጊዜ እንኳን ደስ ያለህ በኀዘኑ ጊዜ ደግሞ እግዚአብሔር ያበርታህ ለማለት ካልጣርን በሚያስፈልገውም ሁሉ የማንረዳው ከሆነ «ሁል ጊዜ አስብሃለሁ» ማለት ብቻ ምን ይጠቅመዋል:: በዚህ መልኩ መራራቅ የሞት ያህል ነውና ያረሳሳል:: ፍቅርንም ያጠፋል እንጂ መተሳሰብም አይባልም:: ፈጣሪንም ቢሆን ጠዋት ማታ ካልጸለዩ፣ ካላመሰገኑት፣ ካልለመኑት፣ ሕጉን ካላከበሩ «አስብሃለው» ቢሉት ጨርሶ በዚህ አይደሰትም::

የያዕቆብ ልጅ ዮሴፍ የጠጅ አሳላፊዎችን አለቃ «ነገር ግን በጎ ነገር በተደረገልህ ጊዜ እኔን አስበኝ» ሲል ምን ማለቱ ነበር? «ምሕረትን አድርግልኝ፥ የእኔንም ነገር ለፈርዖን ንገረህ ከዚህ ቤት አውጣኝ» በማለት በግፍ ከተጣለበት ወኅኒ ቤት እንዲያስወጣው መናገሩ አልነበረም? ዘፍ40÷14 ስለዚህ «በጕብዝናህ ወራት ፈጣሪህን አስብ» ማለትም አንድ ተገቢ ነገር ሥራ ማለት ነው እንጂ በሕሊና ፈጣሪህን አሰላስለው ማለት ብቻ እንዳልሆነ መረዳት ያስፈልጋል::

ከጌታችን ፞መድኃኒታችን ከኢየሱስ ክርስቶስ ቀኝ ተሰቅሎ የነበረው ሽፍታ «አቤቱ በመንግሥትህ በመጣ ጊዜ አስበኝ» ሲል ምን ማለቱ ነበር? ጌታ የማያውቀው ሆኖ ራሱን ማስተዋቁ ነበርን? ወይስ ፈጣሪ በመጣ ጊዜ «አስበኝ ብለኸኝ ነበር» እንዲለው ብቻ ነበርን? ይቅርታ እንዲያደርግለትና መንግሥቱን እንዲያወርሰው መለመኑ እንደ ነበር አያጠራጥርም:: ሉቃ23፥42-43 ታዲያ የ«ማሰብ» ትርጓሜ እንዲህ ከሆነ «በጉብዝናህ ወራት ፈጣሪህን አስብ» ሲባልም ሕጉን ጠብቅ፣ ጸልይ፣ አመስግን፣ ማለት መሆኑ ግልጽ ነው::

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ «አቤቱ በመንግሥትህ በመጣ ጊዜ አስበኝ» በማለት ለለመነው ወንበዴ «እውነት እውነት እልሃለው ዛሬ በገነት ከእኔ ጋር ትኖራለህ» ብሎ የመለሰለት መልስ «ማሰብ» የሚለውን ቃል በሌላ መልኩ እንድናየው ግድ ይለናል:: «አስበኝ» ላለው ወንበዴ «ከእኔ ጋር ትኖራለህ» ካለው «ማሰብ» ማለት ከራስ ጋር አብሮ ማኖር የሚል ትርጓሜ እንዳለው ያስረዳል:: ፊያታዊ ዘየማንም (በቀኝ የተሰቀለው ሽፍታም) «አስበኝ» ሲል «ከራስህ ጋር አኑረኝ» ማለቱ እንደ ነበር ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ «ከእኔ ጋር ትኖራለህ» በማለት ከመለሰለት መልስ እንገነዘባለን:: ሉቃ23፥42-43

ከላይ በተሰጠው ሐተታ መሠረት «ማሰብ» ማለት «ከራስ ጋር ማኖር» ማለት ከሆነ «በጉብዝናህ ወራት ፈጣሪህን አስብ» ማለት ምን ማለት ሊሆን ይችላል? በጉብዝናህ ወራት ፈጣሪህ ካንተ የማይለይበትን ሥራ አድርግ ማለት ነው:: ማለትም ሰውን ከፈጣሪው የሚለየው ኃጢአት ነውና ከኃጢአት ሽሽ! ኢሳ59፥2 በአንጻሩ ደግሞ መልካም ሥራን ሁሉ አድርግ:: በደልህን ሁሉ አምነህ ንስሐ ግባና ቅዱስ ሥጋውንና ክቡር ደሙን ተቀበል:: በዚህ እግዚአብሔር ከአንተ ጋር ይሆናል:: ዮሐ6፥56 ይህን ሁሉ አድርገህ እግዚአብሔር ከአንተ





ጋር ሲሆን «በጉብዝናህ ወራት ፈጣሪህን አስብ» የሚለውን ትእዛዝ በእውነት የፈጸምክ ትሆናለህ::

አኮቴት ወክብር ለሥሉስ ቅዱስ ለአብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ ለዘአፈጸሙኒ በዳኅና ይእዜኒ ወዘልፈኒ ወለዓለመ ዓለም አሜን!

## ዋቢ መጻሕፍት


1. መጽሐፍ ቅዱስ (ሰማንያ ወአሐዱ በአማርኛ) 1980 ዓ.ም ናይሮቢ
2. አርባዕቱ ወንጌል (ንባቡና ትርጓሜው) ትንሣኤ ማተሚያ ቤት 1988 ዓ.ም አ.አ
3. ተግሣጽ ዘቅዱስ ዮሐንስ አፈ ወርቅ ተስፋ ገ/ሥላሴ ማተሚያ ቤት 1987 ዓ.ም አ.አ
4. መዝሙረ ዳዊት ንባቡና ትርጓሜው ተስፋ ገ/ሥላሴ ማተሚያ ቤት 1982 ዓ.ም አ.አ
5. ትንቢተ ሕዝቅኤል ንባቡና ትርጓሜው (ኪዳነ ወልድ ክፍሌ) 1916 ዓ.ም
6. መልእክታተ ጳውሎስ (ንባቡና ትርጓሜው) ትንሣኤ ማተሚያ ቤት 1988 ዓ.ም አ.አ
7. መጻሕፍተ ሐዲሳት ሠለስቱ (ንባቡና ትርጓሜው) ትንሣኤ ማተሚያ ቤት 1989 ዓ.ም አ.አ
8. መጽሐፈ ቅዳሴ (ንባቡና ትርጓሜው) ትንሣኤ ማተሚያ ቤት 1988 ዓ.ም አ.አ
9. ሃይማኖተ አበው፣ ትንሣኤ ማተሚያ ቤት 1986 ዓ.ም አ.አ
10. ፍትሐ ነገሥት (ንባቡና ትርጓሜው) ትንሣኤ ማተሚያ ቤት 1995 ዓ.ም አ.አ







11. ተአምረ ማርያም ተስፋ ገ/ሥላሴ ማተሚያ ቤት 1988 ዓ.ም አ.አ
12. መለከት መጽሔት በዋኖስ የኅትመትና የማስታወቂያ ድርጅት የሚዘጋጅ ትምህርታዊ መጽሔት (የተለያዩ እትሞች)
13. ትዳርና ተላጽቆ ኅብረት የሺጥላ (ዲያቆን) 1994 ዓ.ም አ.አ
14. ኦርቶዶክሳዊ የፆታ ትምህርት (በማኅበረ ቅዱሳን) 1997 ዓ.ም
15. መርሐ ጽድቅ ባህለ ሃይማኖት፣ ሞገስ ዕቁበ ጊዮርጊስ (ሊቀ መዘምራን) 1988 ዓ.ም አ.አ
16. መጻሕፍተ መነኮሳት (ማር ይስሐቅ፣ፊልክስዩስ፣አረጋዊ መንፈሳዊ) ተስፋ ገ/ሥላሴ ማተሚያ ቤት 1982 ዓ.ም አ.አ
17. ድርሳነ ሚካኤል ተስፋ ገ/ሥላሴ ማተሚያ ቤት 1992 ዓ.ም አ.አ
18. ገድለ አቡነ ሀብተ ማርያም አዲስ ማተሚያ ቤት 1995 ዓ.ም እ.አ
19. ዘርጋው የአማርኛ መዝገበ ቃላት (ከባሕሩ ዘርጋው) 1994 ዓ.ም
20. መጽሐፈ ሰዋሰው ወመዝገበ ቃላት (ኪዳነ ወልድ ክፍሌ)
21. ድንግልናዊ ሕይወት፣ ሀብተ ማርያም ወርቅነህ (ሊቀ ሥልጣናት) 1956 ዓ.ም አ.አ
22. ሥርዓተ ቤተ ክርስቲያን፣ ክንፈ ገብርኤል አልታዩ (ሊቀ ካህናት) ትንሣኤ ማተሚያ ቤት 1983 ዓ.ም አ.አ

23. የመጽሐፍ ቅዱስ መዝገበ ቃላት (የኢትዮጵያ መጽሐፍ ቅዱስ ማኅበር) 1972 ዓ.ም አ.አ

24. ፍኖተ አእምሮ (ልዑል ራስ ከሳ ኃይሉ) አርቲስቲክ ማተሚያ ቤት 1953 ዓ.ም አ.አ





# ምግበ ነፍስ!

## (ዜና መጽሐፍ)

### 1. «ሕይወተ ወራዙት»:- ክፍል ሁለት

መጽሐፍ በአጠቃላይ ስለ:-

- ባልንጀርነት፣
- ጫት፣ ትንባሆ፣ መጠጥ፣
- ጌጣጌጥ፣ ቁሳቁስና ንብረት፣
- ሥራ (ተግባረ ዕድ)፣
- በአንድ ቦታ ስለ መርጋት፣
- ተውኔት ማለትም ስለ የአካል ብቃት እንቅስቃሴ (ስፖርት) እና ቴአትር
- ዘፈንና ውዝዋዜ ማለትም እስክስታና ጭፈራ (ዳንስ) ...ወዘተ

በአጠቃላይ ከላይ ስለተጠቀሱት ነገሮች ሊኖር ስለሚገባ ተገቢ መንፈሳዊ አመለካከት ሰፊ ሐተታ ይዛ ዝግጅቷ ሙሉ በሙሉ ያጠናቀቀች በመሆኑ በቅርብ ቀን ለንባብ ትበቃለች:: ስለዚህ በተስፋ ይጠብቋት!!!

# በድጋሚ ዜና መጽሐፍ!

## 2. «ትዳርና ተላጽቆ» ደግሞ ስለ፡-

- ጋብቻ ምንነት፣
- ሠርግ
- በቬሎ ስለ መሞሸር፣
- ከጋብቻ በኋላ ለሰላም መደፍረስ መንሥኤ የሚሆኑ ነገሮችና መፍትሔዎቻቸው
- ሥርዓትን የተከተለ የባልና የሚስት ሩካቤ አፈጻጸምና ጊዜያቶቹ
- እርግዝናን ስለ መከላከልና ... ወዘተ ቀኖና ቤተ

ክርስቲያንና መጽሐፍ ቅዱስ ምን እንደሚሉ ሰፊ ሐተታ በመስጠት የምታብራራ መጽሐፍ ናት።

«ትዳርና ተላጽቆ»፡- ምንም እንኳን ከአንዴም ሁለት ጊዜ የታተመች ብትሆንም እጅግ መካሪና አወያይ ሆና በመገኘቷ በአጭር ጊዜ ውስጥ ከገበያ ጠፍታለች። ስለሆነም ከአንባብያን በተሰጠኝ ጥቆማ መሠረት በጥቂት ቀናት ውስጥ «**ለሦስተኛ ጊዜ**» ለንባብ እንደምትበቃ ለማሳወቅ እወዳለሁ።

